# የአማርኛ  ቋንቋ ትምህርት ተከታታይ ምዘና የአተገባበር ሂደት ፍተሻ፤ በቡኖ በደሌ ዞን በተመረጡ ሶስት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች: ተተኳሪነት


በ

ሳራ ጉታ



ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የማህበራዊ ሳይንስና ስነ-ሰብ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል


የሁለተኛ ድግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊል ማሟያነት

የቀረበ ጥናት


ሰኔ 2011 ዓ.ም

ጅማ፣ ኢትዮጵያ

# የአማርኛ  ቋንቋ ትምህርት ተከታታይ ምዘና የአተገባበር ሂደት ፍተሻ፤ በቡኖ በደሌ ዞን በተመረጡ ሶስት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች: ተተኳሪነት

በ

ሳራ ጉታ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የማህበራዊ ሳይንስና ስነ-ሰብ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

የሁለተኛ ድግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊል ማሟያነት

የቀረበ ጥናት

አማካሪ

ጌታቸዉ አንተነህ (ዶ/ር)

ሰኔ 2011 ዓ.ም

ጅማ፣ ኢትዮጵያ

## ምስጋና

በቅድሚያ የዚህን ጥናት ርዕስ አቅጣጫ ከማስያዝ ጀምሮ ረቂቁን ጽሁፍ ያለምንም መታከት ደጋግመው በማንበብ ቃላትና ሀረጋቱ ተቃንተው መልእክት ማስተላለፍ እንዲችሉ ድጋፍ ላደረጉልኝና ገንቢ ምክራቸው ላልተለየኝ አማካሪዬ ዶ/ር ጌታቸው አንተነህ ከልብ የመነጨ የአክብሮት ምስጋናዬ ይድረስልኝ፡፡ በማስከተልም ለጅማ ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ትምህርት ክፍል ዕድሉን ስለሰጠኝ አመሰግናለሁ፡፡ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በመስጠት ለተባበሩኝ የጅማ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ቤተ-መፃህፍት ሰራተኞች ምስጋናዬ ይድረሳቸዉ፡፡

መረጃዎችን በማሰባሰብበት ጊዜ ለረዱኝ የጥናቱ ተተኳሪ መምህራንና ተማሪዎች፣ የቦረቻ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር አቶ ሚሊዮን ሶሮማ፣ የእንግቢ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር አቶ አበበ ዋቆያ እንዲሁም የገቺ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር አቶ አዲሱ ስኞራ ከልቤ አመሰግናቸዋለሁ፡፡ ምንም እንኳን አስተዋጽኦ የነበራቸውን ሁሉንም መጥቀስ ባይቻልም ጥናቱን በማካሂድበት ወቅት ለነሱ መስጠት ያለብኝ ጊዜ ለጥናቴ በሰጠሁበት ጊዜ ሁሌም ከጎኔ ላልተለየኝ ባለቤቴ አንተነህ ላቀዉ፣ ለልጄ ሂልዳና አንተነህ እንዲሁም ለቤተሰቦቼ በሙሉ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ በአጠቃላይ የኔን ስኬት ማየት ለሚጓጉ የስራ ባልደረቦቼ በሙሉ ምስጋናዬ ወደር የለዉም፡፡

# አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተከታታይ ምዘና የአተገባበር ሂደት ፍተሻ ላይ ያተኮረ ሲሆን የተካሄደዉም በቡኖ በደሌ ዞን በተመረጡ ሶስት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ነዉ፡፡ የጥናቱ ዋና አላማ በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና የአተገባበር ሂደት ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነዉ፡፡ ይህን ጥናት ከግብ ለማድረስ ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በክፍል ውስጥ ምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት አማካኝነት የተሰበሰበዉ መረጃ በዓይነታዊ የትንተና ዘዴ ተተንትኗል፡፡ ይህም በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች መምህራን ተማሪዎቻቸዉን ለመመዘን ምን ዓይነት ስልት እንደሚጠቀሙ እንዲሁም ከማስተማር ሂደት በፊት፣በመማር ማስተማር ሂደት እና ከማስተማር በኃላ የመምህራን የተከታታይ ምዘና የአተገባበር ሂደት ምን እንደሚመስል ተተንትነዋል፡፡ በጥናቱ መረጃ መሰረት የተገኘ ዉጤት የሚያመለክተዉ መምህራን ሳምንታዊ የትምህርት ዕቅድ በማዉጣት ክፍል ዉስጥ በሚገቡበት ወቅት ምን ዓይነት የተከታታይ ምዘና ስልቶችን መተግበር እንዳለባቸዉ ቢዘጋጁም ከ 2(28.57%) መምህራን በስተቀር የተከታታይ ምዘና ሂደቶችም ሆነ ስልቶችን በትክክል ሥራ ላይ አያዉሉትም፡፡ ለዚህም እንቅፋት ከሆኑት መካከል የተማሪዎች ክፍል ውስጥ መብዛት፣የክፍል ምቹ አለመሆን፣የመምህራን የክፍለ ጊዜ መብዛትና የመምህራን ለተከታታይ ምዘና ሂደት ትኩረት አለመስጠት ተጠቃሽ ናቸዉ፡፡ በአጠቃላይ በተካሄደዉ ጥናት የውጤት ትንተና የሚያመላክተዉ የተከታታይ ምዘና በአግባቡ እየተተገበረ አለመሆኑን ነዉ፡፡ ስለሆነም የቡኖ በደሌ ዞን ትምህርት ፅህፈት ቤት ከኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት መስተዳድርና መንግስታዊ ያልሆኑ ደርጅቶች ጋር በመቀናጀት በቂ የመማሪያ ክፍሎች እንዲሰሩ በማድረግ የማስተማሪያ ክፍሎች ምቹ ቢደረጉና በክፍል ዉስጥ የተማሪዎች ቁጥር ቢቀንስ፣የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን በማብዛት የክፍለ ጊዜ መብዛት ጫና መቀነስ፣ የግንዛቤ እጥረት ላለባቸዉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና ስልጠና በየጊዜዉ ቢሰጥ፣የተከታታይ ምዘናዉ በዕቅድ ቢመራ እንዲሁም መምህራን ሁሉንም የምዘና ስልቶች ቢተገብሩ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የሚታዩትን ክፍተቶች ሊሞሉ ይችላሉ፡፡

## ማውጫ

ይዘት ገጽ

ምዕራፍ አንድ፦መግቢያ ........ 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 2
1.3. የጥናቱ ዓላማ ........ 3
1.3.1. የጥናቱ ዋና ዓላማ ........ 3
1.3.2. የጥናቱ ዝርዝር አላማዎች ........ 3
1.4. የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች ........ 3
1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 4
1.6. የጥናቱ ወሰን ........ 4
1.7. የቁልፍ ቃላት ብያኔ ........ 4
ምዕራፍ ሁለት፦ክለሳ ድርሳናት ........ 6
2.1. ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ........ 6
2.1.1.የተከታታይ ምዘና ምንነት ........ 6
2.1.2. የተከታታይ ምዘና ባህሪያት ........ 7
2.1.2.1. የተከታታይ ምዘና ስርዓታዊ ነው ........ 8
2.1.2.2. የተከታታይ ምዘና የተደጋጋሚ ጊዜ የምዘና ውጤት ነው ........ 8
2.1.2.3. ተከታታይ ምዘና ሁሉን አቀፍ ነው ........ 8
2.1.2.4. የተከታታይ ምዘና አቅጣጫ ጠቋሚ ነው ........ 9
2.1.3. የተከታታይ ምዘና ዓላማ ........ 9
2.1.4. የተከታታይ ምዘና አተገባበር ........ 9
2.1.5. የተከታታይ ምዘና የሂደት ደረጃዎች ........ 11
2.1.6. የአጠቃላይና የሂደታዊ ተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ........ 12
2.1.7. ተከታታይ ምዘናን ለመጠቀም የሚያስፈልጉ ምክንያቶች ........ 19
2.1.8. የግብረ-መልስ ምንነት ........ 21
2.1.8.1. የማወዳደር ግብረ-መልስ ........ 22
2.1.8.2. የውጤቶች ወይም የሂደት ግብረ-መልስ ........ 22

2.1.8.3. ገላጭ ወይም ግምገማዊ ግብረ-መልስ ..... 23
2.1.9. ብዙ ተማሪዎች ባሉበት ክፍል ውስጥ የተከታታይ ምዘና አተገባበር ..... 23
2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ..... 25
ምዕራፍ ሶስት፡-የጥናቱ ንድፍና ዘዴ ..... 28
3.1. የጥናቱ ንድፍ ..... 28
3.2. የጥናቱ አካባቢ ..... 28
3.3. የተጠኝ መረጣና የናሙና ዘዴ ..... 29
3.3.1. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ..... 29
3.3.2.የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ ..... 29
3.3.3. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ..... 29
3.3.4. የመምህራን ናሙና አመራረጥ ..... 30
3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ..... 30
3.4.2. የክፍል ምልከታ ..... 30
3.4.2. ቃለ-መጠይቅ ..... 30
3.4.3. የቡድን ተኮር ውይይት ..... 31
3.5. የመረጃ ትንተና ስልት ..... 32
ምዕራፍ አራት፡-የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ ..... 32
4.1. የመረጃ ትንተና ..... 32
4.1.1. የክፍል ውስጥ ምልከታ መረጃ ዉጤት ትንተና ..... 33
4.1.2. የመምህራን ቃለ-መጠይቅ መረጃ ዉጤት ትንተና ..... 43
4.1.3. የተማሪዎች ቃለ-መጠይቅና የቡድን ተኮር ውይይት ..... 39
4.2. የውጤት ማብራሪያ ..... 51
ምዕራፍ አምስት፡-ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች ..... 52
5.1. ማጠቃለያ ..... 52
5.2. የመፍትሄ ሀሳቦች ..... 54
ዋቢ ጽሑፎች ..... 55
አባሪዎች ..... 60

# የሰንጠረዥ ማውጫ


| ርዕስ | ገጽ |
| --- | --- |
| ሰንጠረዥ 1፦ከማስተማር ሂደት በፊት የመምህሩን ተግባር | 33 |
| ሰንጠረዥ 2፦በመማር ማስተማር ሂደት የመምህሩን ተግባር | 34 |
| ሰንጠረዥ 3፦የተከታተይ ምዘና ዘዴዎች መጠቀም | 36 |
| ሰንጠረዥ 4፦ምጋቤ ምላሽ (አስተያየት) መስጠት | 38 |

## የአባሪዎች ማውጫ


ርዕስ ገጽ

አባሪ 1፡ለመምህራን የቀረቡ የቃለ-መጠይቅ ጥያቄዎች ........ 60

አባሪ 2፡ለተማሪዎች የቀረቡ የቃለ-መጠይቅ ጥያቄዎች ........ 61

አባሪ 3፡የቡድን ተኮር ውይይት ጥያቄዎች ........ 63

አባሪ 4፡የክፍል ውስጥ ምልከታ መከታተያ ቅፅ ........ 63

አባሪ 5፡የክፍል ውስጥ ምልከታ ........ 64

አባሪ 6:በቃለ-መጠይቅ የተሳተፉ መምህራን ዝርዝር ........ 71

አባሪ 7:በቃለ-መጠይቅ የተሳተፉ ተማሪዎች ዝርዝር ........ 71

አባሪ 8:በቡድን ተኮር ውይይት የተሳተፉ የቦረቻ ት/ቤት ተማሪዎች ........ 72

አባሪ 9:በቡድን ተኮር ውይይት የተሳተፉ የገቺ ት/ቤት ተማሪዎች ........ 73

አባሪ 10:በቡድን ተኮር ውይይት የተሳተፉ የእንግቢ ት/ቤት ተማሪዎች ........ 71

አባሪ 11:የቡድን ተኮር ዉይይት ተሳታፊዎች ልዩ ልዩ ፎቶ-ግራፎች ........ 76

## ማረጋገጫ

**እኔ ስሜ ከዚህ በታች የተጠቀሰዉ፣ ያቀረብኩት ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ የግል ስራዬ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸውን ዋቢ ፅሁፎች በአግባቡ የጠቀስኩ መሆኔን በፍርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡**

**ስም** **ፊርማ** **ቀን**

_______________ _______________

_______________

ጥናቱ ተገቢ ማሻሻያ የተደረገበት በመሆኑ ገቢ ይሁን፡፡

## የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

**አማካሪ** **ፊርማ** **ቀን**

_______________ _______________

_______________

**የዉስጥ ፈታኝ** **ፊርማ** **ቀን**

_______________ _______________

_______________

**የዉጭ ፈታኝ** **ፊርማ** **ቀን**

_______________ _______________ _______________

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

የትምህርት ምዘና የትምህርት ሥርዓትን በተመለከተ ለውሳኔ የሚረዳ መረጃ የመሰብሰቢያ ሂደት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ስለ መርሃ ትምህርት(Cirriculum) እና መርሃ ግብሩ ፣ ስለመምህራን የትምህርት አሰጣጥና የተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ፣ ስለትምህርት ፖሊሲ ለመወሰን የሚያስችል መረጃ የመሰብሰብ ሂደት ነው (Nitko,1996)፡፡ በመሆኑም የትምህርት ምዘና በተለያየ መልኩ ይካሄዳል፡፡ ይኸውም ፤ የአንድን ሀገር የትምህርት ሥርዓት በመፈተሽ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ለምሳሌ (በየሶስት ወይም በየአራት ዓመት) አንድ ጊዜ የሚካሄድ ሀገር አቀፍ ጥናት፣ በአንድ የትምህርት እርከን ማጠናቀቂያ ለምሳሌ በአንደኛ ወይም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ላይ የሚሰጡ ሀገር አቀፍ ፈተናዎች እንዲሁም በመምህራን የሚካሄዱ ተከታታይ ምዘናዎች የትምህርት ምዘና አካሎች ናቸው (Ministry of Education. 2003).

ከፍ ብሎ እንደተገለጸው ተከታታይ ምዘና መምህራን በክፍል ውስጥ መተግበራቸው ለመምህራንም ሆነ ለተማሪዎች ለተለያዩ ነገሮች እንደሚያግዛቸው ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ትምህርት ሚኒስተር በኢትዮጵያ የትምህርት ስርዓት ዉስጥ ማለትም በዩኒቨርቲዎች፣ በኮሌጆች፣ በአንደኛ ደረጃና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በተለያዩ የትምህርት አይነቶች የተከታታይ ምዘና በክፍል ውስጥ መተግበር እንዳለበት በፖሊሲ ደረጃ ቀርጾ በማስቀመጥ ተግባራዊ መደረግ እንዳለበት በግልጽ ያስገነዝባል፡፡ (Ministry of Education. 2003).

ይሁን እንጂ ይህ የተከታታይ ምዘና እየተሰራበት ቢገኝም የተለያዩ የአተገባበር ችግሮች እንዳሉበት ብዙ አጥኚዎች ይፋ አድርገዋል፡፡ ለምሳሌ፡ መሀመድ (2002) "በደሴ ከተማ በመንግስትና በግል ትምህርት ክፍል በሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መካከል የተከታታይ ምዘና አተገባበር በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት ላይ የአተገባበር ችግር እንዳለበት ጠቁሟል፡፡ እንዲሁም ተስፉ (2000) "የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራን

የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ፤ በትግራይ ክልል በሚገኙ ሦስት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች፡፡” በሚል ርዕስ ባደረጉት ለሁለተኛ ድግሪ ማሚያነት ጥናታቸው ላይ በተመሳሳይ መልኩ የተከታታይ ምዘና የአተገባበር ችግሮች እንዳሉበት ጠቁመዋል፡፡

ከላይ በተለያዩ ምሁራን የተገለፁት ነጥቦች ላይ በመመርኮዝ በኢትዮጵያ ውስጥ የተከታታይ ምዘና መምህራን በክፍል ውስጥ መተግበራቸው ከፍተኛ አስተዋፅኦ ቢኖረዉም የተከታታይ ምዘናዎችን ተግባራዊ ማድረግ ላይ ክፍተቶች እንዳሉ በግልጽ ያስገነዝባል፡፡

እነዚህ ከላይ የቀረቡትን ጥናታዊ ፅሁፎች ትኩረት ያደረጉት በአማራና ትግራይ ክልሎች

የተከታታይ ምዘና ምን እንደሚመስሉና የአተገባበር ችግሮች እንዳሉበት የተጠቆመበት ነዉ፡፡ከዚህም ሌላ ጥናቶቹ ያተኮሩት በሌላ የክፍል ደረጃ በተለይም የኮሌጅና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ነዉ፡፡

ይህንን መነሻ በማድረግ የዚህ ጥናት የትኩረት አቅጣጫ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተከታታይ ምዘና የአተገባበር ሂደት በመፈተሽ የተከታታይ ምዘና ምን እንደሚመስልና በኦሮሚያ ክልል፣ በቡኖ በደሌ ዞን በተመረጡ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ዉስጥ የአተገባበር ችግሮች እንዳሉ ለማረጋገጥ የተሰራ ነዉ፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚዋ ጥናታዊ ጽሁፏን ለማዘጋጀት ስታስብ በቅድሚያ በተለያዩ ከፍተኛ ተቋማት በአማርኛ ቋንቋ የተሰሩ የቅድመ ምረቃ እና የድህረ ምረቃ ጥናታዊ ፅሁፎችን በስፋት ለመፈተሽ ሞክራለች፡፡ በተገኘዉ መረጃ መሰረትም አብዛኞቹ ጥናታዊ ፅሁፎች ያተኮሩት በተከታታይ ምዘና የአተገባበር ሂደት ላይ ሳይሆን በተከታታይ ምዘና ንፅፅራዊ ጥናት ላይ ነዉ፡፡ ከዚህም ሌላ የተከታታይ ምዘና መምህራን በክፍል ዉስጥ መተግበራቸዉ ከፍተኛ አስተዋጥኦ ቢኖረዉ አጥኚዋ ከተለያዩ መምህራን ጋር መደበኛ ያልሆነ የልምድ ልውውጥ በምታካሂድበት ጊዜ ይህንን ተግባራዊ ማድረግ ላይ ክፍተቶች እንዳሉ ተረድታለች፡፡ ለአብነትም መምህራኑ ተከታታይ ምዘናን የሚተገብሩት የቡድን ስራዎችንና በመጨረሻዉ

መንፈቀ ዓመት የሚሰጡ ፈተናዎች ብቻ ላይ በማተኮር ውጤት ለመያዝ እንደሚገለገሉበት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በመሆኑም ይህ አተገባበር አጥኚዋ ካላት የተከታታይ ምዘና ግንዛቤ ጋር የሚቃረን ሁኖ አግኝታዋለች፡፡ እነዚህ የተጠቀሱት ምክንያቶች ዋነኛ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ናቸዉ፡፡ በተጨማሪም አጥኚዋ ከማስተማር ልምዷ የተነሳ ብዙውን ጊዜ መምህራን የሚሰጡት የተከታታይ ምዘና የፅሁፍ ፈተናዎች ላይ ያተኮረ መሆኑን ተረድታላች፡፡ ስለዚህ የተጠቀሱትን አነሳሽ ምክንያቶች መሰረት በማድረግ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተከታታይ ምዘና የአተገባበር ሂደት ፍተሻ፤ በቡኖ በደሌ ዞን በተመረጡ ሶስት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት ጥናት ተደርጓል፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

### 1.3.1 የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና የአተገባበር ሂደት ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነዉ፡፡

### 1.3.2. የጥናቱ ዝርዝር አላማዎች

የጥናቱ ዝርዝር አላማዎች የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

ሀ. በቡኖ በደሌ ዞን በተመረጡ ሶስት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ ተከታታይ ምዘና ያላቸው ግንዛቤ መገምገም፤

ለ. በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለመመዘን የሚጠቀሟቸውን ስልቶች መፈተሽ፤

ሐ. በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተከታታይ ምዘናዎችን ሲተገብሩ የሚያጋጥሟቸው ችግሮች መለየት ናቸዉ፡፡

## 1.4 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

የሚከተሉት መረሰታዊ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

ሀ. በቡኖ በደሌ ዞን በተመረጡ ሶስት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን ስለ ተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት ያላቸው ግንዛቤ ምን ይመስላል?

ለ. በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለመመዘን የሚጠቀሙባቸዉ ስልቶች የትኞቹ ናቸዉ?

ሐ. በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተከታታይ ምዘናዎችን ሲተገብሩ የሚያጋጥሟቸው ችግሮች ምን ምን ናቸው?

## 1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡

በጥናቱ ተተኳሪ የሆኑ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበራቸው እስከምን ደረጃ እንደሆነ የሚያሳይ በመሆኑ በዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀትና አተገባበር ጊዜ የሚታዩትን ስህተቶች በመለየት ለወደፊት የተሻለ ዕቅድ ለማዘጋጀት ብሎም የተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት እውን ለማድረግ በሚደረገው ጥረት ተማሪዎቻቸውን እንዴት መመዘን እንዳለባቸው መረጃ ሊሰጥ ይችላል፡፡ በሌሎች ትምህረት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን በሚኖራቸዉ የማስተማር ህይወት ትክክለኛውንና የተሻለውን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት እንዲጠቀሙበት መረጃ በመስጠት የተከታታይ ምዘና ግንዛቤያቸዉ ሊጨምር ይችላል፡፡ ከዚህም ሌላ የተከታታይ ምዘና መምህራን በክፍል ዉስጥ መተግበራቸዉ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ስላለዉ የጥናቱን ዉጤት ትምህርት ቤቶች፣ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና የዘርፉ ምሁራን ልጠቀሙበት ይችላሉ፡፡ በአጠቃላይ በመስኩ ሰፋ ያለ ጥናት ለማድረግ ለሚፈልጉ አጥኚዎች

እንደ መነሻ በመሆን በተዛማጅ ጽሁፍነት የሚያበረክተው ፋይዳ ሊኖር እንደሚችልም ይገመታል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ያተኮረዉ በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና የአተገባበር ሂደት ምን እንደሚመስል መፈተሽ ላይ ብቻ ነዉ፡፡ ይህም በቡኖ በደሌ ዞን በተመረጡ ሶስት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ማለትም በቦረቻ፣እንግቢና ገቺ ትምህርት ቤቶች የተወሰነ ነዉ፡፡ ከተከታታይ ምዘና ዓይነቶች ዉስጥ ሂደታዊ የተከታታይ ምዘና ላይ ያተኩራል፡፡ በመሆኑም በተጠቀሱት ትምህርት ቤቶች መምህራን ከማስተማር ሂደት በፊት፣በመማር ማስተማር ሂደት እና ከማስተማር በኃላ ያለዉን የተከታታይ ምዘና የአተገባበር ሂደት የዳሰሰ ነዉ፡፡

## 1.7. የቁልፍ ቃላት ብያኔ

በዚህ ጥናት ውስጥ ያገለገሉ ቃላት በጥናቱ ውስጥ ያላቸውን አገልግሎት መሰረት በማድረግ የሚኖራቸው ፍች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ምዘና**

ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ምን እንዳገኙና የትምህርት አቀባበሉን የሚያዳብር ሲሆን በተለያዩ ስልቶች ማለትም በሙከራ፣ ምልከታ፣ በቡድን ስራ፣ በክፍል ስራ፣ በቤት ስራ ወዘተ ስለተማሪዎች የመማር ዕድገት መረጃ መሰብሰብ፣ ማደራጀትና ትርጉም መስጠትን የሚያመለክት ፅንሰ ሀሳብ ማለት ነዉ፡፡

**ሰነደ ትምህርት**

በተከታታይ ምዘና ሂደት ተማሪዎች በተለያዩ ጊዜያት እየሰሩ ያጠራቀሟቸው የተለያዩ ክምችት ማለት ነዉ፡፡

**ተለምዷዊ ምዘና**

በፅሁፍ ፈተና ላይ ብቻ ያተኮረ የምዘና ስልት ሆኖ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀመው ተማሪው አልፏል ወይስ ወድቋል ብሎ ውሳኔ መስጠት ማለት ነዉ፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

በየጊዜውና በየወቅቱ ተማሪዎች ስርዓተ ትምህርቱ በነደፈው አላማ መሰረት ትምህርቱን መከታተላቸውን መምህሩ የምዘና ስልቶችን በመጠቀም የሚያረጋግጥበት አካሄድ ነዉ፡፡

**ሙከራ**

መደበኛ የሆነ የተማሪዎችን የመማር እድገት ለመለካት የሚያገለግል ሆኖ ከሁለት በማይበልጡ የትምህርት ይዘቶች የሚወጡ ጥያቄዎችና የትምህርት ተግባራት የያዘ የምዘና ስልት ማለት ነዉ፡፡

**ፈተና**

መደበኛ የሆነ ብዛት ያላቸውን የትምህርት ይዘቶችን የሚያካትተውና የተለያዩ የጥያቄ አይነቶችን የያዘ ሲሆን ከአንድ ኮርስ የትምህርት አይነት ወይም ስልጠና ከተጠናቀቀ በኋላ የሚሰጥ የምዘና አይነት ማለ

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በቡኖ በደሌ ዞን፣2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ዘጠነኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና የአተገባበር ሂደት ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነዉ፡፡ ይህን መሠረታዊ ጽንሰ ሀሳብ ለማብራራት በትኩረት ነጥቡ ዙሪያ ያሉ ተዛማጅ ጽሑፎችን ለመዳሰስና ትንታኔ ለመስጠት ጥረት ተደርጓል፡፡

## 2.1. ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

በዚህ ክፍል የተከታታይ ምዘና ምንነት፣ የተከታታይ ምዘና ዘዴዎች፣ የተከታታይ ምዘና ዓላማ፣የተከታታይ ምዘና አስፈላጊነት፣ የተከታታይ ምዘና አተገባበር መጠቀም ያስፈለገበት ምክንያት እንዲሁም ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ተዳሰዋል፡፡

### 2.1.1. የተከታታይ ምዘና ምንነት

ተከታታይ ምዘና ከስሙ መረዳት እንደሚቻለው ከተለያዩ የምዘና ዘዴዎች አንዱና ተከታታይ የሆነ ድርጊትን የሚጠይቅ መሆኑን ያመለክታል (መሀመድ 2002፤7):: ይህንን የምዘና ዓይነት ምሁራን በተለያዩ ስያሜዎች ሲጠሩት 'የክትትል መዝገብ'፣ ስርዓተ ትምህርት ተኮር ምዘና' ወዘተ. በመሳሰሉት ስያሜዎች ይጠራል (በድሩ 1994፤25)፡፡ Abiy (2013)፣ "ተከታታይ ምዘና ብዙ ድርጊቶችን የያዘ ሐረግ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ ይህም ሲታይ ግን በተለያዩ ሁኔታዎች ላይ በማተኮር የተማሪዎችን የዕውቀት' የክህሎትና የዝንባሌ ዝርዝር ባህሪያት መግለጫ በማደራጀት የተማሪዎችን የመማር ተነሳሽነት የሚያጎለብትና የመማር ማስተማሩን ስራ ለማሻሻል የሚረዳ ነው፡፡" ሲሉ ይገልፃሉ፡፡

በተጨማሪም ታጠቁና ሌሎች (1995፤12) እንዳስረዱት ተከታታይ ምዘና እንደ ሂደታዊ ግምገማ (Formative Evaluation) የሚታይ ሆኖ ትኩረቱ ስርዓቱን በጠበቀ መንገድ ተማሪው በዕውቀት በአስተሳሰብና በክህሎት ያገኘውን ለውጥ በየጊዜው ተከታትሎ ለማሳየት የሚረዳ የምዘና ስልት ነው፡፡

Dessalegn (2004፡2) እንደሚገልጹት ደግሞ ተከታታይ ምዘና በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ በልዩ ልዩ ተግባራት (በቤት ሥራ፣ በግል ሥራ፣ በራስ ምዘና ወዘተ) ተማሪውን በማሳተፍ ብቁ የሆነ ክህሎት ይዞ እንዲያድግ ለማድረግ የሚረዳ ነው፡፡ ተከታታይ ምዘና የተማሪውን ብቻ ሳይሆን የመምህሩን የማስተማር ስልት' ዝግጅትና ዕውቀት ከሚገኘው ምጋቤ ምላሽ ለማሻሻል የሚያግዝ ነው ስሉ አጠናክረውታል፡፡ ከዚህ ጋር በማያያዝም Aggrawal (1994፡364) እና ተካ(1998፤20) ተከታታይ ምዘና በፈተና ሊገኙ የማይችሉ ሌሎች ተፈላጊ የባህሪ ክህሎቶች አሉ፤እነዚህ ደግሞ መታወቅና መገምገም ያለባቸው ለስብዕና መዳበር ጠቃሚ የሆኑ ክህሎቶች ናቸው፡፡እነዚህን ባህርያት ለማስገኘት የሚረዳ ስልት ነው ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

በተጨማሪም ተስፋ (2000) ተከታታይ ምዘና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ትኩረት እያገኘ የመጣ የምዘና ስርዓት ነው፡፡ ተከታታይ ምዘና የመማር ማስተማር ሂደት ዋና አካልና ተማሪዎችን በሂደት የመመዘኛ ስልት ሲሆን ዓላማውም ተማሪዎች በሚማሩበት ትምህርት ውጤታማ እንዲሆኑ ማገዝና የመማር ማስተማሩን ሂደት መሻሻል ነው፡፡ ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን አጠቃላይ ዕውቀት ክህሎት አመለካከት የትምህርት አቀባበልና አካሄድ በመመዘን ተማሪዎችን ለማገዝ እንዲሁም በተማሪዎች፣ በመምህራንና በትምህርት ቤቱ ላይ ጠቃሚ ውሳኔ ለመስጠት መረጃ የሚሰበሰብበት የምዘና ሰርዓት ነዉ፡፡

ከላይ የቀረቡትን የተከታታይ ምዘና ትርጓሜዎች የሚከተሉትን ማጠቃለያዎች መስጠት ይቻላል፡፡ ተከታታይ ምዘና የተለያዩ የምዘና መሳሪያዎችን በመጠቀም የተለያዩ የመማሪያ ክፍሎችን የማሰብ ሂደትን ብቻ ሳይሆን ሰብዓዊ ባህሪያትና ግለሰባዊ ገፅታዎችን ለመመዘን የሚያስችል የምዘና አቀራረብ ነው፡፡ በተመሳሳይ ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን ዕውቀት ክህሎት እና አመለካከት ለማሳደግ' የተማሪዎች ተጨማሪ ድጋፍ ለመስጠት መምህራንና ተማሪዎች ሥርዓተ ትምህርቱን ለመከለስ እና ተማሪዎችን ለማነቃቃትና ለማበረታታት ይረዳል ብሎ ማጠቃለያ መስጠት ይቻላል፡፡

### 2.1.2. የተከታታይ ምዘና ባህሪያት

ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን ውጤት ለማወቅ የሚረዳ ሳይሆን ተማሪው በመማር ማስተማሩ ምን እንዳገኘና የትምህርት አቀባበሉን በበለጠ እንዲያዳብር የሚያደርግ መሆኑ ተከታታይ ምዘናን ልዩ የሚያደርጉት አራት መሰረታዊ ባህሪያት አሉት (Selamneh ,2011).

#### 2.1.2.1. የተከታታይ ምዘና ስርዓታዊ ነው

ተከታታይ ምዘና ስርዓት ያለው ነው ሲባል ግልፅ በሆነ እቅድ ያለው ሆኖ መምህራን የተማሪዎችን ችሎታ የሚገመግሙባቸውን የተከታታይ ምዘና መሳሪያዎች ማለትም ከአጫጭር የፅሁፍ ፈተናዎች፣ሙከራ፣የቃል ፈተናዎች፣ የግልና የቡድን ሥራዎች፣ ቃለ መጠይቆችን ወዘተ የሚይዝ እንዲሁም ግምገማዎች የሚደረጉባቸውን ጊዜያት ስርዓትን ተከትለው ተከታታይነት ባለው መልኩ የሚቀርቡበት መሆኑ ነው፡፡ ለተከታታይ ምዘና ዕቅድ ይዘጋጃል፡፡በዕቅዱ መሰረት ይተገበራል፡፡ ዕቅድ በሚዘጋጅበት ጊዜ ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ነገሮች ምዘናው የሚካሄድበት ስልት፣ ጊዜ፣ የሚተኮርባቸው የትምህርት ክፍሎች፣ የውጤት አያያዝ ወዘተ መሰረት አድርጎ ነው፡፡(Selamneh ,2011).

#### 2.1.2.2. የተከታታይ ምዘና የተደጋጋሚ ጊዜ የምዘና ውጤት ነው

በአንድ ተማሪ ላይ የተሟላና ተገቢውን የትምህርት ምስክርነት እና ውሳኔ ለመስጠት በአንድ ጊዜ የሚሰጥ የፈተና ግምገማ በቂ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ስለተማሪው ሁለንተናዊ የአዕምሮ የሙያ ክህሎትና አመለካከት ዕድገት በቂ መረጃ ስለማይስጥ ነው፡፡ በተከታታይ ምዘና አማካይነት የተሰበሰቡ መረጃዎች ተጠናቅረው መቅረብ አለባቸው፡፡ ይህ ካልተደረገ ስለተማሪዎቹ የተሟላ መረጃ ተይዟል ለማለት አይቻልም፡፡ ተከታታይ ምዘና የተደጋጋሚ ጊዜ የምዘና ውጤት ነው ሲባል ተከታታይ ምዘና በባህሪው የተለያዩ የምዘና ስልቶችን ስለሚጠቀም ተማሪው በተለያዩ ጊዜያት የሚያሳየውን አጠቃላይ ባህርያት አጠቃሎ የሚያሳይ ማለት ነው (Brooks, 2002)፡፡

### 2.1.2.3. ተከታታይ ምዘና ሁሉን አቀፍ ነው

ተማሪዎች በትምህርት ቤት ቆይታቸው በቂ ዕውቀት ቀስመው ክህሎታቸውን አዳብረውና አመለካከታቸውን አስፍተው እንዲወጡ ይጠበቃል፡፡ ተማሪዎች ሊማሯቸው የሚገባቸውን እነዚህን ባህርያት በትክክል ለመመዘን በተለያዩ ጊዜያት የሚሰጡ ፈተናዎችና መሳሪያዎች በቂ አይደሉም በእርግጥ በፈተና ዕውቀትንና ክህሎትን መለካት ይቻል ይሆናል፡፡

አመለካከትንና የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ወዘተ ለመለካት ግን ያስቸግራል ፡፡ ተከታታይ ምዘና እንደ ተለምዶአዊው ፈተና በአእምሮአዊ ክህሎት (cognitive skill) ላይ ብቻ የተወሰነ አይደለም ሁለቱንም ማለትም እውቀትንና ክህሎትን እንዲሁም ስሜትን፣ ዝንባሌንና እምነትን ለመመዘን ያስችላል፡፡

### 2.1.2.4. ተከታታይ ምዘና አቅጣጫ ጠቋሚ ነው

ከተከታታይ ምዘና የሚገኘው ውጤት የተማሪዎች የወደፊቱ አቅጣጫ ስለሚጠቁም በመማር ማስተማሩ ሂደት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ በትምህርታቸው ችግር ያላቸውን ተማሪዎች በመለየት ለመርዳት የሚቻለው የተከታታይ ምዘና ውጤትን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ ተከታታይ ምዘና መምህራን የተማሪዎቻቸውን ችግሮች በሚገባ እንዲለዩና አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስዱ የሚያግዝ ነው (Brooks, 2002)፡፡

## 2.1.3. የተከታታይ ምዘና ዓላማ

እንደ Moe (2003፡7) መምህራን ተማሪዎቻቸውን እንዲመዘኑ የሚያደርጉዋቸው ምክንያቶች የሚከተሉት ዓላማዎች መሰረት በማድረግ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ የተማሪዎችን የመማር ሁኔታ ለማሻሻል፡ይህ ማለት የምዘና ውጤቶች ተማሪው እንዴት እየተማረ እንዳለ እና አስተማሪው እንዴት እያስተማረ እንዳለ ምጋቤ ምላሽ ስለሚሰጡ ከምጋቤ ምላሽ የተገኘውን መረጃ የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማሻሻል ያግዛል፡፡ ተማሪዎች የትኛውን ይዘት የበለጠ መማር እንዳለባቸው ለመወሰን፡፡ ተማሪዎች በየትኞቹ የትምህርት ዓይነቶች ጠንካራ እንደሆኑ በየትኞቹ የትምህርት ዓይነቶች ደግሞ ድክመት እንዳሳዩ ለመለየትና ድክመት ባሳዩበተ ትምህረት ላይ የትኩረት አቅጣጫዎን ለመቀየስ፡፡ በአጠቃላይ የተከታታይ ምዘና ዋና ዓላማ የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሁኔታዎችን ለማሻሻልና ተማሪዎችን በሚማሩት ትምህርት ዙሪያ ውጤታማ ማድረግ ነው፡፡

## 2.1.4. የተከታታይ ምዘና አተገባበር

ተከታታይ ምዘና በተማሪዎች ላይ ስለሚታዩ ባህሪያትና ስለአጠቃላይ የመማሪያ ክፍል ሁኔታን አስመልክቶ ተከታታይነት ባለው ሂደት መረጃ የሚሰበሰብበት ሂደት አድርጎ መውሰድ ይቻላል፡፡የተሰበሰቡትን መረጃዎች በማደራጀትና በመተንተን መምህራን ተማሪዎቻቸውን እንዲያውቁ ዕቅዳቸው እንዲያቅዱ የመማር ማስተማር ሂደቱን ለመቆጣጠር ምቹና ጤናማ የመማሪያ ክፍሎች ሁኔታ እንዲፈጥሩ ይረዳቸዋል፡፡ (Capper 1996 Nitko 1996):: በተመሳሳይ ተከታታይ ምዘና ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት ምን ያህል ውጤታማ እንደሆኑ መምህራን ደግሞ የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል ምን ያህል እንደሰሩና ተማሪዎች የራሳቸውን መማር ምን ያህል እንዳሻሻሉ ተደጋጋሚ ምዘና የሚደረግበት ሂደት ነው፡፡ በመሆኑም ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን ተፈላጊውን የመማር ውጤት ምን ያህል እንዳሳኩ ለማረጋገጥ ተማሪዎች ምን መሻሻል እንዳሳዩ ለማረጋገጥ በመማር ማስተማር ሂደት ያጋጠማቸውን ለመለየት የመማር ማስተማር ሥነ-ዘዴዎች ውጤታማነት ለማረጋገጥ እና በመማር ማስተማር ሂደት ላጋጠሙ ችግሮችና እጥረቶች የተወሰዱ እርምጃዎችን ለማረጋገጥ የሚረዱ መረጃዎች የመሰብሰቢያ ሂደት ነው፡፡

የተከታታይ ምዘና ዓይነቶች የሆኑት ሂደታዊና አጠቃላይ ተከታታይ ምዘናዎች በተማሪዎች የመማር ሂደት ውስጥ እንደመማር ማስተማር ሂደት እና እንደ መረጃ መሰብሰቢያ ሂደት ከፍተኛ ጠቀሜት ያለው ሚና ይጫወታሉ፡፡ ሂደታዊ ተከታታይ ምዘና መምህራን ከተማሪዎች ወይም ተማሪዎች ከተማሪዎች በጋራ እና ተማሪዎች በተናጠል ለብቻቸው የሚያከናውናቸው እንዲለዩ፣ አሳታፊ የመማር ማስተማር ሥነ ዘዴ ተማሪዎችን በተግባራዊ የሥራ እንቅስቃሴ እንዲገቡ እና ተማሪዎች በመማር ማስተማር ግቦች ላይ እንዲያተኩሩ ያበረታታል፡፡ ይህ ዓይነቱ የምዘና ስልት መምህራን ከተማሪዎች ጋር በመነጋገር ሥራ ሲሰሩ በመመልከት የስራቸውን ውጤት ያገኛሉ፡፡ ተማሪዎች የሂደታዊ ተከታታይ ምዘና መረጃን የሚያገኙት በግብረ-መልስ መልክ ነው፡፡

## 2.1.5. የተከታታይ ምዘና የሂደት ደረጃዎች

ዳንኤል (1999፣7) እና አልማዝ (2003) ተከታታይ ምዘና በሦስት ደረጃዎች ተከፋፍሎ ሊካሄድ ይችላል፡፡ የመጀመሪያዉ ከማስተማር ሂደት በፊት ሲሆን በዚህ ደረጃ ተከታታይ ምዘና የሚደረግበት ዋና ዓላማ ተማሪዎች በሂደት ስለሚማሩት ምዕራፍ ዋና ርዕስና ንዑስ ርእሶች ያላቸውን ቅድመ ግንዛቤና ልምድ በተመለከተ መረጃ ለመሰብሰብ ነዉ፡፡ ሁለተኛዉ በመማር ማስተማር ሂደት ነዉ፡፡ በዚህ ደረጃ ሂደታዊ ተከታታይ ምዘና የሚተገበርበት ዋና ዓላማ፡- ተማሪዎች የሚማሩት ትምህርት ምን ያህል እየተከታተሉ ናቸው? ምን ያህል እየተረዱ ናቸው? ወዘተ በሚሉ ጉዳዮች ዙሪያ መረጃ ለመሰብሰብ፣ በደንብ እየተከታተሉ ያሉትን ለማበረታታት ይረዳል፡፡ ሶስተኛዉ ደረጃ ከማስተማር በኋላ ሲሆን ተከታታይ ምዘና የሚካሄድበት ዋና ዓላማ በየምእራፉ የተካተቱትን የትምህርት ዓላማዎች መሰረት ባደረገ መልኩ ተማሪዎች ምን ያህል የባህርይ ለውጥ አምጥተዋል? በሚሉ ጥያቄዎች ዙሪያ መረጃ ለመሰብሰብ ነዉ፡፡

## 2.1.6. የሂደታዊ ተከታታይ ምዘና ዘዴዎች

መምህራን ሊጠቀሙባቸው ከሚችሉ የአጠቃላይ ተከታታይ ምዘና ዋና ዋና ዘዴዎች ሁለት ናቸው፡፡ እነሱም የሂደታዊ ተከታታይ ምዘና ዘዴ እና አጠቃላይ ምዘና ዘዴ ናቸዉ፡፡ መምህራን ሂደታዊ ተከታታይ ምዘና በመተግበር ሰፋ ያለ መረጃ ይሰበስባሉ፡፡ ይህም የመማር ማስተማሩን ሂደት ከተማሪዎች የትምህርት

አቀባበል ጋር እንዲጣጣሙ ያግዛቸዋል፡፡ ከዚህ በመቀጠል የሂደታዊ ተከታታይ ስልቶችን እንመለከታለን፡፡

### 1. የቃል ጥያቄ

ይህን የተከታታይ ምዘና ስልት አንድ መምህር በየትኛውም የመማር ማስተማር ሂደት ሊጠቀምበት ይችላል፡፡ ይህ ዓይነቱ ስልት ተማሪዎች የተማሩትን ምን ያህል እንደተገነዘቡትና ተማሪዎች የት ላይ ችግር እንዳለባቸው ለማወቅ ይጠቅማል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ አንድ መምህር የዚህ ዓይነቱን የምዘና ስልት መደበኛ ባልሆነ በመማር ማስተማሩ ሂደት ከተማሪዎች ጋር ተግባቦት ለመፍጠርና ለመመዘን የሚያስችል ነው፡፡ በክፍል ውስጥ የቃል ጥያቄን እንደ አንድ የምዘና ዘዴ የመጠቀም ዋና ዓላማ በመማር ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎችን ትኩረት ወደ ትምህርቱ ለመሳብ እንደሆነ (Elington፣1997፡ 4-15) ይገልፃሉ፡፡

### 2. ምልከታ

ምልከታ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚሰሩትንና የሚናገሩትን በጥሞና በዓይን በመከታተል የምንመዘግብበት ዘዴ መሆኑን Brooks (2002፡5) ይገልፃሉ፡፡ በምልከታ አማካይነት መረጃ ለማግኘት ከተፈለገ መምህራን የምልከታ ክሂል ያስፈልጋቸዋል፡፡ ይህም የምልከታ ክሂል ምን መመልከት እንደሚፈልጉ ማወቅን፣ በጥሞና ማዳመጥን፣ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው በሚያደርጓቸው ተግባቦቶች ላይ ማተኮርን፣ ጠቃሚ ነገሮችን በማስታወሻ መያዝን እና ደግሞ ደጋግሞ ማሰብን ይጠይቃል፡፡

እንደ Brooks (2002፡5) ገለፃ ምልከታ አብዛኛውን ጊዜ መምህራን በክፍል ውስጥ ተማሪዎቻቸውን ለመመዘን የሚጠቀሙበት ዘዴ ነው፡፡ ምልከታ የሚካሄደው በክፍል ውስጥ ተማሪዎች ሲወያዩና የተለያዩ የክፍል ውስጥ ተግባራትን ሲያከናውኑ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውኑ አስተማሪው እየተዘዋወረ በመመልከት እንዲሰሩ፣ የታዘዙትን ተግባራት በትክክል ማከናወናቸውንና በሂደትም ያጋጠሙዋቸውን ችግሮች መጠየቅና መረዳት አለበት፡፡ ስለዚህ ምልከታ የሚካሄደው በክፍል ውስጥ

ተማሪዎች ሲወያዩና የተለያዩ የክፍል ውስጥ ተግባራትን ሲያከናውኑ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

### 3. ቅድመ ፈተና

ለማስተማር በምናቅድበት ጊዜ ተማሪዎቻችን ስለምናስተምረው ርዕስ ምን ያህል ግንዛቤ እንዳላቸው ትምህርቱን ማስተማር ከመጀመራችን በፊት ማወቅ መቻል አለብን፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ስለርዕሱ ያላቸውን የቀደመ ግንዛቤ ለማወቅ ከተወሰነ ጊዜ ቀደም ብሎ ለተማሪዎች የቅድመ ግንዛቤ ፈተና መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ከቅድመ ግንዛቤ ፈተና የተገኘው ውጤት አስተማሪው ለወደፊት ለማስተማር የሚጠበቅበትን ትምህርት በአግባቡ እንዲያቅድና የተለያዩ የምዘና ተግባራትን በዕቅዱ ውስጥ እንዲያካትት ዕድል ይፈጥርለታል፡፡

### 4.የቤት ሥራ

የቤት ሥራ ተማሪዎች የተማሩትን ይዘት በሚገባ እንዲለማመዱ የሚያግዝ የምዘና ስልት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቤት ሥራ አንድ አስተማሪ ተማሪዎቹን ምን ያህል ትምህርቱን እየተከታተሉ እንደሆነ የሚያረጋግጥበት ስልት ነው፡፡ የቤት ሥራ ከሂደታዊ የምዘና ስልቶች መካከል አንዱ ሲሆን ተማሪዎች የትኞቹን ርዕሶች ደግመው መማር እንዳለባቸውና እንደሌለባቸው የእርምት ምጋቤ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የምዘና ስልት ነው፡፡

### 5. ፈተና እና ሙከራ

ፈተና እና ሙከራ በቋንቋ ክፍል ውስጥ ተማሪዎችን ለመመዘን ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡ በፈተና እና በሙከራ መካከል የተወሰነ ልዩነት እንዳለ Teshome,(2001) ሲገልፅ አንድ መምህር ፈተና ለመፈተን በሚያስብበት ጊዜ ለተማሪዎቹ አስቀድሞ ይነግራቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የፈተና የትኩረት አቅጣጫ በተወሰኑ ይዘቶች ላይ ነው፡፡ በሙከራ ጊዜ ግን መምህሩ ሙከራ ለተማሪዎች እንደሚሰጥ አይነግራቸውም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለተማሪዎች የሚሰጠው ሙከራ በንግግር ወይም በጽሁፍ መልክ ሊቀርብ ይችላል፡፡

ከትምህርቱ ዓላማ ጋር ግንኙነት ያላቸውና በጥንቃቄ የተዘጋጁ የቋንቋ ፈተናዎችና ሙከራዎች በተማሪዎቹ አዕምሮ ውስጥ አዎንታዊ አመለካከት

እንዲፈጠር ያደርጋሉ፡፡ በተገቢው ሁኔታ የተዘጋጁ ፈተናዎችና ሙከራዎች የተማሪዎችን በርትቶ የማጥናት ስሜት ይቀሰቅሳሉ፡፡ እንዲሁም በጥንቃቄ የተዘጋጁ ፈተናዎች ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ዙሪያ ያሉባቸውን ችግር እንዲለዩና በየትኞቹ ርዕሶች ላይ በርትተው መስራት እንደሚገባቸው አስፈላጊውን መረጃ እንደሚሰጡ ነዉ (Teshome, 2001)፡፡

በእያንዳንዱ ምዕራፍ ማጠቃለያ ላይ የሚሰጡት ፈተናዎች ለመምህራንና ለተማሪዎች የሚሰጡት መረጃ ጠቃሚ ናቸዉ፡፡ ነገር ግን ፈተናዎች ተማሪዎች የመንፈቂን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ የሚሰጡ ከሆነ መምህሩ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ማስተካከል ስለሚገባው ነገር የሚሰጡት መረጃ የዘገየ ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም መምህሩ ፈጥኖ ለተማሪዎች ተገቢውን ምጋቤ ምላሽ ላይሰጥ ይችላል፡፡ ከዚህ ሀሳብ ጋር ተያያዥነት ባለው መልኩ Teshome (2001:28) Salem (1989) ስራዎችን በመጥቀስ በመንፈቅ ማጠቃለያ ላይ የሚሰጡትን ፈተናዎች ተማሪዎች ማሻሻል የሚገባቸውን በመጠቆም በኩል የሚያበረክቱትን አስተዋፅኦ የጎላ ነው፡፡ ምክንያቱም ፈተናዎች የሚሰጡት በትምህርቱ መጨረሻ ላይ ስለሆነ ነው ይላሉ፡፡

ፈተናዎችና ሙከራዎች ተማሪዎች አንድ ምዕራፍ ከመጨረሳቸው በፊት የሚሰጡ ከሆነ ግን ለመምህራንና ለተማሪዎች ስለመማር ማስተማሩ ሂደት የሚያስተላልፉት መረጃ በጣም ጠቃሚ እና ሂደቱን የሚያግዝ ይሆናል፡፡ በመሆኑም መምህራን ከፈተናዎችና ከሙከራዎች የተገኙትን መረጃዎች መሰረት በማድረግ ተማሪዎች በየትኞቹ ርዕሶች ላይ ጥንካሬ እንዳሳዩ በየትኞቹ ርዕሶች ላይ ደግሞ ድክመት እንዳሳዩ መለየት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ፈተናዎችና ሙከራዎች በተከታታይ ምዘና ሂደት የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማገዝና ስለተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል የተከታታይ ምዘና ስልቶች መሆናቸውን ይገልፃሉ፡፡ MOE.(1994).

### 6.የቡድን ስራዎች

ተማሪዎች የተማሩትን ነገር ምን ያህል በተግባር ላይ እንደሚያውሉት ለማወቅ የሚካሄድ የምዘና ስልት መሆኑን Birhanu (2004) ይገልፃሉ፡፡ የቡድን ሥራ

በሚሰጥበት ጊዜ የእያንዳንዱን ተማሪ ሥራ ይታረምና ውጤት ይሰጠዋል፤ ውጤቱም ይመዘገባል፡፡ በመሆኑም በተከታታይ ምዘና ውስጥ አንድ ዘዴ ወይም ስልት ነው ማለት ይቻላል፡፡ የቡድን ሥራ ለተማሪዎች በሚሰጥበት ጊዜ በጥንቃቄ ማቀድና ማሰብን ይጠይቃል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች በግልም ሆነ በቡድን አንድ ሥራ እንዲያከናውኑ ማድረጉ የተማሩትን ነገር ምን ያህል ተግባራዊ እንደሚያደርጉት ለማወቅ እና ሀሳባቸውን በግልፅ እንዲያንፀባርቁ ለማድረግ እንደሚረዳቸው ይገልፃሉ፡፡

በአጠቃላይ ውጤታማ የቡድንና የግል ሥራ በሚከተሉት ነገሮች ላይ ይመሰረታሉ፡፡ ግልፅ የሆኑ ተግባራትን በመስጠት፣ ግልፅ የሆኑ የመመዘኛ መስፈርቶችን በማውጣት፣ ፍትሀዊ (Fair) ውጤት በመስጠት፣ ከትምህርቱ ዓላማ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተግባራትን በመቅረፅ፣ በመሆኑም ውጤታማ የቡድን ሥራ ለማካሄድ ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች ሁሉ ቢሟሉ ተማሪዎች በሚሰሩት ሥራ እርካታ ያገኛሉ፡፡

## 7. የመምህር ተማሪ ውይይት

የመማር ማስተማሩን ሥራ በተመለከተ በመምህርና በተማሪ መካከል የሚካሄዱ ውይይት አንድ የምዘና ዘዴ ነው፡፡ በተማሪዎችና በመምህራን መካከል የሚካሄድ ውይይት ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት ምን ያህል መሻሻል እንዳሳዩ ለመምህሩ ጥሩ የሆነ አዕምሮአዊ ምስል ከመስጠቱም በላይ በውይይቱ ጊዜ ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ በማድረግ በኩል ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው Birhanu (2004). ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም በመምህርና በተማሪ መካከል የሚካሄድ ውይይትና ቃለ መጠይቅ በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት ተማሪዎች ያሳዩትን መሻሻል ኢ-መደበኛ መልኩ የምንመዝንበት ስልት ነው፡፡ በመምህር በተማሪ መካከል የሚካሄድ ውይይት አንድ ተማሪ በትምህርቱ ምን ያህል ውጤታማ እንደሆነና ፍላጎቱ ምን እንደሆነ ለመመዘን ያስችላሉ፡፡

## 8. ሰነደ ትምህርት

ሰነደ ትምህርት ማለት ተማሪዎች በተለያዩ ጊዜያት ያከናወኗቸው ሥራዎች ስብስብ ወይም ክምችት ሲሆን ተማሪው በሚማረው የቋንቋ ትምህርት ዙሪያ ምን መሻሻሎችን እንዳሳዩ ለመምህሩ አዕምሮአዊ ስዕል የሚሰጥ የምዘና ስልት መሆኑን Elington and Earl (1997፡7) ይገልፃሉ፡፡

ሰነደ ትምህርት ተማሪዎች በተለያዩ ጊዜያት እየሰሩ ያስቀመጧቸው የተለያዩ ሥራዎች ክምችት በመሆኑ ተማሪዎች ያዳበሯቸውን ክሂሎች በተመለከተ በስፋው መረጃ ይሰጣል፡፡ ሰነደ ትምህርት የተማሪዎች የቀደመ ዕውቀት ምን እንደነበርና አሁን ደግሞ በምን ደረጃ ላይ እንዳለ ለማወቅና የተማሪዎችን ዕውቀትና ክሂል ምን እንደሆነ አጉልቶ ስለሚያንፀባርቅ ለአስተማሪው ጥሩ መረጃ ስለሚሰጥ ተማሪው ረዘም ላለ ጊዜ ያሳየውን ግለሰባዊ ዕድገት ስለሚያንፀባርቅ ከሌሎች የተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ይልቅ ስለተማሪው ሁለንተናዊ ባህሪ አስተማማኝ መረጃ ይሰጣል፡፡

ይሁን እንጂ እንደ Elington and Earl (1997፡8) ሰነደ ትምህርት ያሉት ደካማ ጎኖች የእያንዳንዱን ተማሪ ሰነደ ትምህርት አንብቦ ለተማሪዎች ገንቢ አስተያየት ለመስጠት ጊዜ መዉሰዱ እና የሰነደ ትምህርት ሥራዎች በውስጣቸው የተለያዩ ተግባራትን ስለሚይዙ እያንዳንዱን መስፈርት ተግባር አውጥቶ ለመመዘን ይከብዳል፡፡ በመሆኑም ሰነደ ትምህርት የራሱ የሆኑ ጠንካራና ደካማ ጎኖች እንዳሉዋቸው አውቀው መምህራን በተገቢ ሁኔታ እንደአንድ የምዘና ዓይነት ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡

## 9. የራስ ምዘና

ከምዘና ሂደት ውስጥ አንዱ ዘዴ የራስ ምዘና ነው፡፡ የራስ ምዘና ማለት ተማሪዎች የራሳቸውን ጠንካራና ደካማ ጎን በራሳቸው የሚገመግሙበት ስልት ነው፡፡ እንደ Puhi (1997፡10) ገለፃ ተማሪዎች በተወሰነ ትምህርት ላይ ትኩረት ሰጥተው ከሰሩ በኋላ ምን ያህል ውጤታማ እንደሆኑ ራሳቸውን ይመዝናሉ፡፡ ይህ ምዘናም ያሳዩትን መሻሻል እንዲገነዘቡ ያስችላቸዋል፡፡ እንደ Puhi (1997፡10) ገለፃ ተማሪዎች የራሳቸውን የትምህርት ሂደት በራሳቸው ሊመዝኑ የሚችሉት

አስፈላጊ ሁኔታዎች ከተሟሉላቸው ነው፡፡ ከነዚህም አስፈላጊ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ተማሪዎች ራሳቸውን በራሳቸው እስከአሁን ደህና አድርጌ የሰራሁት ምንድን ነው? በሚቀጥለው ማሻሻል ያለብኝ ምንድን ነው? ጠንካራና ደካማ ጎኔ የት ላይ ነው? ብለው ለመመዘን መስፈርቶች ያስፈልጋቸዋል፡፡

እንደ Hamis (1997፡10) ገለጻ የራስ ምዘና ተማሪዎች በራስ የመተማመን ችሎታቸው እንዲያጎለብቱና ግልፅነትን እንዲላበሱ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ደካማና ጠንካራ ጎናቸውን ለይተው በማውጣት ለድክመቶቻቸው ማስተካከያ የሚሆን መንገድ እንዲቀይሱና ችግሮቻቸውን ለመቅረፍ የሚያስችል እርምጃዎች እንዲወስዱ ያስችላቸዋል፡፡ ራስን መመዘን ተማሪዎች ለትምህርታቸው ከፍተኛ ሀላፊነት እንዲሰማቸው ያደርጋል፡፡

## 10. የጓደኛ ለጓደኛ (የቢጤ) ምዘና

በተከታታይ ምዘና ሂደት ተማሪዎችን ለመመዘን ከምንጠቀምባቸው የምዘና ስልቶች አንዱ የቢጤ (የጓደኛ ለጓደኛ) ምዘና ነው፡፡ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ከቢጤዎቻቸው (ከጓደኞቻቸው) ጋር በመሆን ሥራዎቻቸውን እርስ በርሳቸው የሚመዘኑበት ጠቃሚ የሆኑ የማሻሻያ ሀሳቦችን ከጓደኞቻቸው የሚቀስሙበት የምዘና ስልት የቢጤ ምዘና እንደሚባል Puhi (1997፡4) ይገልፃሉ፡፡

የቢጤ ምዘና ለተማሪዎች ስለሚሰጠው ጥቅም Puhi (1997፡7-8) የሚከተሉትን ነገሮች አቅርቧል፡፡ በቢጤ ምዘና ዓውድ ውስጥ ተማሪዎች በሚሳተፉበት ጊዜ ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን የተለያዩ የምዘና መስፈርቶችን እንዲያወጡ ያስችላቸዋል፡፡ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው ምጋቤ ምላሽ እንዲሰጣጡ ያስችላቸዋል፡፡ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው ሀሳባቸውን በነፃነት እንዲያንፀባርቁ ያስችላቸዋል፡፡ ተማሪዎች እንዲነቃቁ ያደርጋቸዋል፡፡ ተማሪዎች ነገሮችን ከተለያዩ አቅጣጫ የማየትና አመዛዝኖ የማሰብ ችሎታን ያጎለብትላቸዋል፡፡ አስተማሪዎች የተማሪዎቻቸውን ሥራ በማረም የሚያጠፉትን ጊዜ ይቀንስላቸዋል፡፡

ምንም እንኳን የቢጤ ምዘና ከላይ የተጠቀሱት ጠቀሜታዎችና ጠንካራ ጎኖች ቢኖሩትም ደካማ ጎኖች ደግሞ አሉት፡፡ ተማሪዎች እርስበርስ የመተራረም ችሎታ ላይኖራቸው ይችላል፡፡ በጓደኛሞች መካከል በጣም የመቀራረብ ሁኔታ ስለሚኖር ተማሪዎች በትክክል የጓደኞቻቸውን ሥራዎች ላይመዝኑ ይችላሉ፡፡ አንዳንዴ ተማሪዎች ጓደኞቻቸው የሚሰጧቸውን አስተያየት አምነው ላይቀበሉት ይችላሉ፡፡ስለሆነም ምንም እንኳን የቢጤ ወይም የጓደኛ ለጓደኛ ምዘናን መጠቀሙ ከላይ የተገለፁት ደካማ ጎኖች ቢኖሩትም፤ መምህራን በተከታታይ ምዘና ሂደት ምዘናን አዘውትረው መጠቀም አለባቸው፡፡ ይህንን ለማድረግ የቢጤ ምዘናን ዓላማና ጥቅም ለተማሪዎቻቸው ግልፅ ማድረግ እንዳለባቸው ነው፡፡

### 11. እየወጡ ማቅረብ ምዘና

Birhanu,(2004). እንደሚገልፁት፣ የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ለማወቅ ከምንጠቀምባቸው የምዘና ስልቶች መካከል አንዱ እየወጡ ማቅረብ ነው፡፡ እንደ ምሁሩ ገለፃ ከቋንቋ ትምህርቱ ጋር በተያያዘ መልኩ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን እየወጡ እንዲያቀርቡ በማድረግ መመዘን የተለያዩ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን እየወጡ በሚያቀርቡበት ጊዜ መምህራን የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታና አጠቃቀም መመዘን ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን እየወጡ በሚያቀርቡበት ጊዜ መምህራን የተማሪዎችን የሀሳብ አደረጃጀት መመዘን ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን እየወጡ በሚያቀርቡበት ጊዜ መምህራን የተማሪዎችን ፍላጎት መመዘን ይችላሉ፡፡ በአጠቃላይ መምህራን በቋንቋ ክፍል ውስጥ የተማሪዎችን የተለያዩ የክፍል ውስጥ ተግባራትን እየወጡ እንዲያቀርቡ በማድረግ የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ፣ ፍላጎት፣ የሀሳብ አደረጃጀት ችሎታ ወዘተ መመዘን ይችላሉ፡፡

## 2.1.7. ተከታታይ ምዘናን ለመጠቀም የሚያስፈልጉ ምክንያቶች

ተከታታይ ምዘና ያስፈለገበት ዋና ምክንያት የትምህርት ዓላማዎችን የአመለካከት ዓላማዎችን ጨምሮ የምዘና ክህሎቶችና የቡድን ሥራን በመጠቀም ለመመዘን እንዲቻል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ተከታታይ ምዘና በትምህርት ቤቶች የመማር ማስተማር ሂደቱን ለማሻሻል ይረዳል፡፡ Nejabli (1987) ተከታታይ ምዘና ማካሄድ ያስፈለገበትን ዋና ምክንያት ፤ አንድ ፈተና በመስጠት

ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ወይም ችግር ለማጥፋት ወይም ለመቀነስ እንዲቻልና የተማሪዎችን ስኬታማነት በተመለከተ ትክክለኛ አመላካች ለማስቀመጥ ነው፡፡ ምክንያቱም ተከታታይ ምዘና በንቃት በመማር ማስተማር ሥራ የተሳተፈ ማንም ተማሪ ሊወድቅ አይገባም የሚል አስተሳሰብ ስለሚይዝ ነው በማለት ገልጿል፡፡

እንደ ገለጻው ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን ስኬታማነት ዕውቀትንና ክህሎትን መመዘንን ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡ በተጨማሪም መምህራንና ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት ወቅት ምን ባህርይ እንደነበራቸው በመከታተል አስተያየት መስጠት አለባቸው፡፡ ይህም መምህራን በተማሪዎች ሁለንተናዊ የምዘና ሂደት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በከፍተኛ ደረጃ እንዲሳተፉ የሚያደርግ በመሆኑና ስለተማሪዎች ሁለንተናዊ ችሎታና ውጤታማ የሥራ አፈፃፀም ትክክለኛ ምዘና ሊሰጥ በመቻሉ ነው፡፡ በመጨረሻም ተከታታይ ምዘና መምህራን በመማር ማስተማር ሂደት የራሳቸውን የማስተማር ሥነ-ዘዴ እንዲያሻሽሉ መሠረት የሚጥል ነው፡፡

## 2.1.8. የግብረ-መልስ ምንነት

ግብረ-መልስ ለመሻሻል የሚጠቀምበት መረጃ ነው፡፡ ግብረ-መልስ መምህራንና ተማሪዎች በመማር ሂደት የሚያከናውኗቸውን ተግባራት፣ የሠሯቸውን ሥራዎች እና የሰጡትን መልስ በመመርመርና በመተንተን ያገኙትን ለተማሪዎች መልሰው የሚያሳውቁበት መንገድ ሲሆን መረጃውም ተማሪዎች አፈፃፀማቸውን ወይም ክንዋኔያቸውን እንዲያውቁ ይረዳቸዋል፡፡ ይልቁንም ጥሩ ግብረ - መልስ የተማሪዎችን ሥራ ገላጭ ነው፤ በክንዋኔና በዝርዝር ዓላማ ላይ የተወሰነ ነው፤ ተማሪው እንዴት እንደሚሻሻል የሚደረግለት ድጋፍ የያዘ ነው፡፡ ግብረ-መልስ ጥንካሬን፣ መሻሻልን የሚፈለገውንና የማሻሻያውን ዘዴ የሚያሳይ ነው፡፡ ጥሩ ግብረ-መልስ ተማሪው የሚጠቀምበትን መረጃ የያዘ ነው፡፡ ይህ ማለት መጀመሪያ ተማሪዎች ግብረ-መልሱን ሊሰሙትና ሊረዱት የሚችሉት መሆን አለበት፡፡ ከግንዛቤአቸውና ከአቅማቸው በላይ የሆነን ነገር አይሰሙም፡፡

በተመሳሳይ ማዳመጥ የማይፈልጉትን ነገር አይሰሙም ወይም ጠቃሚ አይደለም ብለው ካሰቡትም አያዳምጡትም፡፡ በጣም ጠቃሚ ግብረ-መልስ የተማሪዎችን

የሥራ ጥራት ወይም ሥራው የሚሰራበት ሂደትና ስትራተጂዎች ላይ ያተኩራል፡፡ የተማሪው ትኩረት ወደ እራስን መምራት ስትራተጂ ወይም ችሎታዎች የሚስብ ግብረ-መልስ ጠቃሚ ነው፡፡ መምህራን ለተማሪዎች የሚሰጡት የግብረ-መልስ ዓይነት በመምህራን የማስተማር ሁኔታ ይወሰናል፡፡ ግብረ-መልስ ለመስጠት ዓላማ ሊኖር ይገባል፡፡ ግብረ-መልሱም ከተማሪዎችና ከመማር ማስተማር ሥነ-ዘዴዎች/ዘይቤዎች ጋር መዛመድ ይኖርበታል (Birhanu,2004).

Nitko (2008) ሦስት ዓይነት የግብረ-መልስ አሰጣጥ እንዳለ ይገልፃሉ፡፡ እነርሱም የማወዳደር (የማነፃፀር) ግብረ-መልስ፣ የውጤቶች ወይም የሂደቶች ግብረ-መልስ እና የገላጭ ወይም የግምገማ ግብረ-መልስ ናቸው፡፡ እነዚህ እንደሚከተለው በዝርዝር እንመለከታቸዋለን፡፡

### 2.1.8.1. የማወዳደር ግብረ-መልስ

ግብረ-መልስ በሚሰጥበት ወቅት ከሚተገበረው የንፅፅር ዓይነቶች አኳያ ይለያያል፡፡ ለተማሪዎች ንፅፅራዊ ግብረ-መልስ ለመስጠት ሦስት መሰረታዊ መንገዶች አሉት፡፡ በተማሪዎች የእርስ በርስ የችሎታ ንፅፅር ላይ የተመሰረተ ግብረ-መልስ፡ የተማሪው/ዋን ሥራ ከተማሪዎች ሥራ ጋር ያነፃፅራሉ፡፡ ለምሳሌ የውሀ ውህድ ሥዕልህ/ሽ ከክፍሉ ተማሪዎች እጅግ በጣም ጥሩ ነው፡፡ የተማሪዎችን ሥራ ከዝርዝር ዓላማው ጋር በማነፃፀር ተማሪዎች ማድረግ ያለባቸውንና የሌለባቸውን ይነግራቸዋል፡፡ ለምሳሌ አንተ/አንቺ በባለአራት አሃዝ የማባዛት ችሎታህ/ሽ በጣም ጥሩ ነው፡፡ ለምሳሌ ይህ ህይወት ያላቸው እና የሌላቸው ዝርዝር ከዚህ በፊት ከሠራኸው የተሻለ ነው፡፡ ጥሩ የሚባለው የሂደታዊ ተከታታይ ምዘና ግብረ-መልስ ተማሪዎች እየተማሩ የሚሰጥ በመስፈርት የተመሰረተው ግብረ-መልስ ነው፡፡ በክፍል ውስጥ ከሚገኙ ተማሪዎች ስለራሳቸው ችሎታ እርግጠኛ ላልሆኑና ለመማር በቂ ችሎታ የለንም ብለው ለሚያስቡ ተማሪዎች በራስ ላይ የተመሰረተ ግብረ-መልስ መጠቀም ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም ምን ያህል እንደተሻሻሉ እንደሆኑ ለማሳየት ይችላል (ኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ፣ 2004)፡፡

### 2.1.8.2. የውጤቶች ወይም የሂደት ግብረ-መልስ

ግብረ-መልስ ከሚገልጸው የተማሪ ውጤቶች አንፃር ወይም ተማሪው/ዋ አንድ ሥራ ለመፈፀም ከተከተለው/ችው ዘዴ አንፃር ይለያያል፡፡ ማለትም የሚሰጠው ግብረ-መልስ የተማሪዎችን የሥራ ውጤት አሠራር ላይ ወይም ተማሪው ሥራውን ለመስራት የሄዱበትን መንገድ ላይ ሊመረኮዝ ይችላል፡፡ የውጤት ግብረ-መልሰ የመምህራን ግምገማ ተማሪው/ዋ ያገኘው/ችው ውጤት ላይ ብቻ በማተኮር ግብረ-መልስ ይሰጣል፡፡ የዚህ ዓይነት ግብረ-መልስ አሠጣጥ የመምህሩ/ሯን ግምገማ በተማሪው/ዋ ሥራ ብቻ የተመሰረተና የውጤቱን ማጠቃለያ ብቻ ለተማሪው/ዋ የሚነገረው፡፡ ግምገማው ከሚጠበቀው ውጤት አንፃር ምን ያህል እንደተማሩ፣ ምን ያህል እንዲሻሻል እና ምን እንደሚያሻሽሉ ለተማሪዎች አይገለፅም (Frans,2007)፡፡

በሌላ በኩል በግንዛቤ ላይ ያተኮረ ግብረ-መልስ (Cognitive feedback) ተማሪው/ዋ ሥራውን ለመስራት በተከተለው ዘዴ እና ያገኘው/ችው ውጤት መካከል ያለውን ግንኙነት ለተማሪው/ዋ ይገለጻል፡፡ በዚህም ሥራው የሚሻሻልበትን መንገድ ይመራል፡፡ የተሻለ ግብረ-መልስ የሚባለው የግንዛቤ ግብረ-መልስ ነው፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ለማሻሻል ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንዲያውቁ ይረዳቸዋል፡፡ የውጤት ግብረ-መልስ በጣም ውሱን ነው፡፡ የውጤት ግብረ-መልስ ተማሪው/ዋ እንዳያሻሽል ወይም እንድታሻሽል የሚረዳው/ዳት ተማሪው/ዋ ለራሱ/ሷ የግንዛቤ ግብረ-መልስ መስጠት ከቻለ ብቻ ነው (Frans,2007)፡፡

### 2.1.8.3. ገላጭ ወይም ግምገማዊ ግብረ-መልስ

የዚህ ዓይነቱ ግብረ-መልስ አሠጣጥ ገላጭ እና ግምገማዊ ግብረ-መልሶችን ያካተተ ነው፡፡ በገላጭ ግብረ-መልስ ተማሪው/ዋ በሠራው/ችው ሥራ ላይ ሥራውን በተመለከተ ለተማሪው/ዋ መረጃ ይሠጣል፡፡ ለምሳሌ፡በድርሰትህ ውስጥ የድርጊት ገላጭ ቃሎች አጠቃቀምህን/ሽን ወድጄዋለሁ፡፡ ይህ ዓይነት ግብረ-መልስ አሰጣጥ ተማሪው/ዋ በሠራው/ችው ሥራ ያለውን መልካም ነገር በመግለፅ

ተማሪው/ዋ ከተቀመጠው መስፈርት አኳያ ምን ያህል እንደሠራ/ች ያመለክታል (Frans,2007)፡፡

በግምገማዊ ግብረ-መልስ ሥራውን በተመለከተ የመምህሩ/ሯ ውሳኔ ምንም ዓይነት ተጨማሪ የሥራውን ጥራት የሚያሳይ ሳይኖር ለተማሪው/ዋ ይገለፃል፡፡ ለአብነት በሥራው 60% አግኝተሀል/ሻል ወይም በጣም ጥሩ ሥራ ነው፡፡ ይህ ግብረ-መልስ ጥሩ ሥራ ስለተባለው ምን ነገር ጥሩ እንዳደረገው አይገለፅም፡፡ ተማሪው/ዋ ሥራውን ለምን እንደሆነ ከግምት ያለፈ ማስተካከያ ሊወስድ ወይም ልትወስድ አይችልም/ትችልም፡፡ ተማሪዎች የበለጠ ጥሩ ሆኖ የሚያገኙት መምህራን ገላጭ የሆነ ግብረ-መልስ ሲሰጧቸው እንጂ ግምገማዊ ግብረ-መልስ ሲሰጧቸው አይደለም፡፡ ምክንያቱም በገላጭ ግብረ-መልስ ለተማሪዎች የሚሰጠው ግብረ-መልስ ተማሪዎች የሰሩት ሥራ ከተቀመጠው መስፈርት ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ሊነገራቸው ይገባል (Frans,2007)፡፡

## 2.1.9. ብዙ ተማሪዎች ባሉበት ክፍል ውስጥ የተከታታይ ምዘና አተገባበር

ምዘና በሂደት እየተካሄደ እንደሆነና የመማር ማስተማር ዓላማ መሳካት ወይም አለመሳካት ለማረጋገጥ የሚረዳ ሁሉንም ዘዴዎች ያካተተ ነው፡፡ ምዘና ያለምንም ጥርጥር በትክክል ሊለኩ የሚችሉ የሂደት ክፍሎችና ውጤቶችን እንዲሁም ግላዊ ሀሳብን የያዙ የምዘና ውሳኔን ይጨምራል፡፡ ተከታታይ ምዘና ወይም ያለማቋረጥ በሂደት ላይ የሚካሄድ እና የአጠቃላይ ወይም በመጨረሻ ላይ (ማጠናቀቂያ ምዕራፍ) የሚካሄድ የምዘና ክፍሎች ናቸው፡፡ የተማሪዎች ቁጥር በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ተፅእኖ እንደሚያሳድረው ሁሉ በምዘና ዘዴዎችም ላይ የራሱ ተፅእኖ ያሳድራል፡፡ በአሁኑ ወቅት ያለ የትምህርት ጽሁፎች ብዙ ተማሪዎች ካሉበት የመማሪያ ክፍሎች ጋር በተያያዘ በርካታ የምዘና ጉዳዮችን ለይተዋል፡፡ እነርሱም የሚከተሉትን ያካትታል፡፡(Birhanu Moges,2004)

ብዙ ተማሪዎች ባሉበት ክፍል የሚኖሩ የምዘና መርሆች በሌሎች ክፍሎች ላይ ተግባራዊ ሊደረጉ የሚችሉ ናቸው፡፡ መምህራን በመማሪያ ክፍላቸው ያሉ የተማሪዎች ብዛት ግምት ውስጥ ሳያስገቡ ጥራት ያለውና በትክክል የተካሄደ

ምዘና እንዲኖር ይፈልጋሉ፡፡ የተሻለ ምዘና የሚባለው ለተቀመጠለት ዓላማ ትክክለኛ፣ አስተማማኝ እና ተገቢ ሲሆን ነው፡፡ ምዘናው ከተማሪዎች ውጤታማነት በመነሳት ሠርተፍኬት ለመስጠት ወይም ምደባ ለማካሄድ የሚያስችል ሊሆን ይችላል ወይም የተማሪዎች መማርና ግንዛቤ ለማመቻቸት የሚረዳ ይሆናል፡፡ (Birhanu Moges, 2004)

## 2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ይህንን ጥናታዊ ጽሁፍ ለመስራት ሌሎች ለዚህ ጥናት ርዕስ ጋር የተሻለ ቅርበት ያላቸው ጥናታዊ ፅሁፎች እንደሚከተለው ተቃኝተዋል፡፡

የመጀመሪያዉ የተዛማጅ ጽሁፍ በታምሩ ፀጋዬ (2004 ዓ.ም) የቀረበ ሲሆን የጥናቱ ርዕስም "የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ ሦስት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች" የሚል ነው፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኮሌጅ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው፡፡ ይህንን ዓላማ ለማሳካት የጽሁፍ መጠይቅ፣ ቡድን ተኮር ውይይት፣ ሰነድ ፍተሻና ምልከታን ተጠቅሟል፡፡ በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፈጣንና በቂ ግብረ-መልስ እንደማይሰጡ፣ የተማሪዎቻቸው የግልና የቡድን ስራዎች ሲያርሙ መስፈርት እንደማይጠቀሙና የተከታታይ ምዘና ዕቅድ እንዳላካተቱ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡

ይህን ጥናት ከላይ ከተጠቀሰዉ ጥናት ጋር የሚያመሳስለውም ሆነ የሚለየው መንገድ አለ፡፡ ከሚያመሳስላቸው ስንነሳ የታምሩ ጥናት ከዚህ ጥናት የሚመሳሰልበት በተከታታይ ምዘና አተገባበር በመሆኑ፣ምልከታ እና ቡድን ተኮር ውይይት እንደ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት በመገልገሉ ነዉ፡፡ በተጨማሪም ይህንን ጥናት ከላይ ከተጠቀሰዉ ጥናት ጋር የሚለየውን መንገድ ስንመለከት በመጀመሪያ የታምሩ ጥናት ትኩረት በኮሌጅ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ምን እንደሚመስል መፈተሽ ሲሆን፣ የዚህ ጥናት ትኩረት ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ

መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት ምን እንደሚመስል መፈተሽ በመሆኑ፣ የጥናቱ ትኩረት ይለያል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የታምሩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የጽሁፍ መጠይቅና ሰነድ ፍተሻ ሲሆኑ የዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ደግሞ ቃለ መጠይቅ፣ ምልከታ እና ቡድን ተኮር ውይይት በመሆናቸው በዚህ ይለያሉ፡፡

ሁለተኛዉ የተዛማጅ ጽሁፍ በአልማዝ ፍሬው (2003 ዓ.ም) የቀረበ ሲሆን የጥናቱ ርዕስም "በአማራ ክልል በሚገኙ ሁለት የመንግስት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ" የሚል ሲሆን የጥናቱ ዋና ዓላማ በኮሌጅ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተከታታይ ምዘና እንዴት እንደሚተገብሩ መመርመር ነው፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት የክፍል ውስጥ ምልከታ፣ የጽሁፍ መጠይቅ፣ የሰነድ ፍተሻና ቃለ መጠይቅን እንደ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት በመጠቀም ጥናቱ ተጠናቋል፡፡ የጥናቱ መረጃ መተንተኛ ዘዴዎች ደግሞ አሃዛዊና ዓይነታዊ የመተንተኛ ዘዴዎች ሲሆኑ የጥናቱ ውጤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አዘውትረው የሚጠቀሙባቸው የተከታታይ ምዘና መሳሪያዎች የቡድን ስራ፣ የቃል ጥያቄ፣ እየወጡ ማቅረብና የክፍል ስራ ሲጠቀሙ የቢጤ ግምገማና የሚና ጨዋታ ወዘተ የማይጠቀሙባቸው መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡

ይህን ጥናት ከላይ ከተጠቀሰዉ ጥናት ጋር የሚያመሳስለውም ሆነ የሚለያየው መንገድ አለ፡፡ይሄዉም የዚህ ጥናት ትኩረት ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት ምን እንደሚመስል መፈተሽ በመሆኑ፣ የጥናቱ ትኩረት ይለያል፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ደግሞ የክፍል ውስጥ ምልከታ፣ የጽሁፍ መጠይቅ፣ የሰነድ ፍተሻና ቃለ መጠይቅ በመሆናቸው በዚህ ይለያሉ፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት ደግሞ ቡኖ በደሌ ዞን፣ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት ምን እንደሚመስል መፈተሽ ስለሆነ በርዕስና በአላማ ቢመሳሰልም በቦታና በጥናት ጊዜ ይለያያሉ፡፡

ሶስተኛዉ የተዛማጅ ጽሁፍ በአልማዝ ሀይሌ (1999 ዓ.ም) የቀረበ ሲሆን ይህ ጥናት አማርኛን በማስተማር ስነ ዘዴ ለማስተርስ ድግሪ ሟሟያ የቀረበ ነው፡፡ የጥናቱ ርዕስም "አራተኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ የሚል ነው፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማም የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል የ4ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር መመርመር ነው፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት የሰነድ ፍተሻ፣ ምልከታ፣ የጽሁፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ እንደ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት በመጠቀም ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ በጥናቱ ግኝት መሰረትም ተጠኚ መምህራን ተከታታይ ምዘናን የሚተገብሩት ተከታታይ ፈተናዎችን በመስጠት እንደሆነ ከጥናቱ አቅራቢ ለማረጋገጥ ችላለች፡፡ በመሆኑም ከዚህ ጥናት ጋር በርዕስ ቢመሳሰልም በጥናቱ ትኩረትና በጥናቱ ዘመን ይለያያል፡፡ በአጠቃላይ በጥናት አቅራቢዎቹ ዉጤት ላይ በመመርኮዝ የተገኙትን መልካም ተሞክሮዎች በመዉሰድና እና የታዩትን ክፍተቶች በመሙላት ይህ ጥናት ተሰርቷል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት
# የጥናቱ ንድፍና ዘዴ

## 3.1. የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በቡኖ በደሌ ዞን፣ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና የአተገባበር ሂደት ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነዉ፡፡ ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም መረጃዎች ተተንትነዋል፡፡ ጥናቱ አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ የአጠናን ዘዴን የተከተለ ነዉ፡፡ ምክንያቱም ይህ የምርምር ዓይነት የአንድን ሁኔታ ትክክለኛ ገጽታ ለማወቅ ወይም በትክክል ለመግለጽ ሲባል መረጃዎችን ከመጽሐፍትና ከሌሎችም ጥናታዊ የጽሑፍ ምንጮች በማሰባሰብና በማጠናቀር ትንተና በማድረግ የሚጠና በመሆኑ ነዉ፡፡ ስለዚህ 9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና የአተገባበር ሂደትን ከተለያዩ አካላት ከሚገኙ መረጃዎች በአግባቡ በመተንተን በገላጭ የምርምር ስልት ለመግለጽ ስለሚያስችል ነዉ፡፡

## 3.2. የጥናቱ አካላይ

ይህ ጥናት ያተኮረዉ በኦሮሚያ ክልል፣ በቡኖ በደሌ ዞን ውስጥ የሚገኙ ሶስት 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ሲሆን ቦረቻ፣እንግቢና ገቺ ትምህርት ቤቶች የጥናቱ አካላይ ናቸዉ፡፡ በሶስቱም 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2011 ዓ.ም የትምህርት ዘመን 9ኛ ክፍል በመማር ላይ የሚገኙ ተማሪዎችንና የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በጥናቱ እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ በአጠቃላይ 64 ተማሪዎችና ሰባት 9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በናሙናነት ተመርጠዉ መረጃ ሰጥተዋል፡፡

## 3.3. የተጠኚ መረጣና የናሙና ዘዴ

### 3.3.1. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

ለዚህ ጥናት ተመራጭ ሆነዉ የተገኙት በኦሮሚያ ክልል፣ በቡኖ በደሌ ዞን ውስጥ የሚገኙ ሶስት 2ኛ ደረጃ ትምርት ቤቶች ቦረቻ፣እንግቢና ገቺ ናቸዉ፡፡ ትምህርት ቤቶቹ አመቺ የናሙና ዘዴን በመጠቀም የተመረጡ ናቸዉ፡፡ የተመረጡበት

ምክንያትም አጥኚዋ በቅርበት የምታውቃቸዉና ሌሎች ትምህርት ቤቶች ርቀት ላይ በመገኘታቸዉ መረጃዎችን በሚፈለገው አኳሃን ሰብስቦ ለማደራጀት አስቸጋሪ እንዳያደርገው በማለት ነዉ፡፡

## 3.3.2. የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

ለዚህ ጥናት የተመረጠዉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነዉ፡፡ የተመረጠበት ምክንያትም አጥኚዋ ከማስተማር ልምዷ የተነሳ ችግሩን በቀላሉ የምትረዳዉ በመሆኑ ሲሆን ሁለተኛ ደረጃ እርከን ካሉት የክፍል ደረጃዎች ውስጥ ደግሞ የተመረጠው የ9ኛ ክፍል ነው፡፡ ይህ የክፍል ደረጃ የተመረጠበት ምክንያትም የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ለሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና ስለሚዘጋጁ መረጃውን ለመስጠት ብዙም ትኩረት እንደማይሰጡ ግምት ውስጥ በማስገባት ነዉ፡፡ በሶስቱም ትምህርት ቤቶች በአጠቃላይ 27 የመማሪያ ክፍሎች ይገኛሉ፡፡ ለክፍል ዉስጥ ምልከታ የተመረጡት አስራ አራት ክፍሎች ናቸዉ፡፡ ይሄዉም ከቦረቻ አራት (9ኛA፣C፣H፣I)፣ ከእንግቢ ስድስት (9ኛA፣D፣F፣G፣H፣I)፣ ከገቺ አራት (9ኛB፣D፣G፣H) ናቸዉ፡፡

## 3.3.3. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

ለዚህ ጥናት በናሙናነት የተመረጡት በ2011 ዓ.ም በቡኖ በደሌ ዞን፣ 2ተኛ ደረጃ ትምርት ቤቶች ቦረቻ፣እንግቢና ገቺ 9ኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች ናቸው፡፡ የ9ኛ ክፍል የተማሪዎች ብዛት ቦረቻ ወንዶች 399፣ ሴቶች 319፣ድምር 718 ፣እንግቢ ወንዶች 328፣ ሴቶች 362፣ ድምር 690፣ ገቺ ወንዶች 295፣ ሴቶች 269፣ ድምር 564 ናቸዉ፡፡ በዚህ ጥናት በአጠቃላይ 64 ተማሪዎች በናሙናነት ተመርጠዉ መረጃ ሰጥተዋል፡፡ ተማሪዎቹን ለመምረጥ ዓላማ ተኮር የናሙና አወሳሰድ ዘዴ ሥራ ላይ ዉሏል፡፡

## 3.3.4. የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በቡኖ በደሌ ዞን፣ 2ኛ ደረጃ ትምርት ቤቶች ቦረቻ፣እንግቢና ገቺ በ2011 ዓ.ም 9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን ብዛታቸው ሰባት ሲሆኑ ጠቅላይ የናሙና አወሳሰድ ዘዴ በመጠቀም ሁሉም በመረጃ ሰጪነት ተሳትፈዋል፡፡ እነዚህም ቦረቻ ትምህርት ቤት ሴቶች 2፣እንግቢ ትምህርት ቤት

ወንዶች 3፣ ገቺ ትምህርት ቤት ሴቶች 2 ናቸዉ፡፡ መምህራን ሲያስተምሩ ያስተዋሏቸውን ችግሮች በቅርበት የሚያውቁትና የስራው ባለቤት በመሆናቸው በመረጃ አቀባይነት አገልግለዋል፡፡ ይህም የሚያገለግለዉ ለተመራማሪው መረጃ ሊያስገኙ የሚችሉ ሰዎች በቁጥር አነስተኛ ወይም ውስን በሚሆኑበት ወቅት ያሉትን ሰዎች ሁሉንም በመውሰድ መረጃ መሰብሰብ ተገቢ በመሆኑ ነዉ፡፡

## 3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ለጥናቱ የተመረጡት ሶስት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

### 3.4.1. የክፍል ምልከታ

ለጥናቱ ከተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መካከል የክፍል ዉስጥ ምልከታ ዋነኛ ሲሆን መምህራን በሚያስተምሩበት የተለያዩ ክፍሎች የተከታታይ ምዘና ሂደትን ለመከታተል የሚጠቅም የመከታተያ ቅጽ በማዘጋጀት አንድ መምህር ለሁለት ጊዜያት በአጠቃላይ ለአስራ አራት ዙር ከቀን 1/08/2011-9/08/2011 ዓ.ም ድረስ ተከታታይ ምልከታ ተደርጓል፡፡ የመማሪያ ክፍሎቹ የተመረጡት ቀላል የዕጣ ናሙና አወጣጥ ዘዴ በመጠቀም ነዉ፡፡ ይህም መምህራን ከማስተማር ሂደት በፊት፣ በመማር ማስተማር ሂደት እና ከማስተማር ሂደት በኋላ የተከታታይ ምዘናን እንዴት እንደሚተገብሩ አመቺ የጊዜ ሰሌዳ በማውጣት ተካሂዷል፡፡ የመከታተያ ቅፁ ተከናውኗል፣ አልተከናወነም የሚል የአማራጭ ደረጃዎችን በመያዙ በሰንጠረዡ ውስጥ ምልክት ተደርጎበታል፡፡ ለምልከታዉ አመቺ ሆነዉ የተገኙት ቀናት ቦረቻ (ረቡዕና አርብ)፣ እንግቢ (ረቡዕ)፣ ገቺ(ማክሰኞና ሐሙስ) ናቸዉ፡፡ እነዚህ ቀናት የተመረጡበት ምክንያትም በየትምህርት ቤቶቹ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በተጠቀሱት ቀናት የሚሰጥ በመሆኑና የምልከታ ክፍለ ጊዜ መደራረብ እንዳይኖር ታሳቢ በማድረግ ነዉ፡፡ የመማሪያ ክፍሎቹ የተመረጡበት ምክንያት ሁሉም ተተኳሪ መምህራን የሚያስተምሩበት ክፍል ስለሆኑ ነዉ፡፡

### 3.4.2. ቃለ-መጠይቅ

በዚህ ጥናት ስራ ላይ ከዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አንዱ ቃለ-መጠይቅ ነው፡፡ በቃለ-መጠይቅ የሚገኙ መረጃዎች ሰዎች የታዘቡትን፣የተገነዘቡትንና

ያዩትን ጉዳዮች አውጥተው ምላሽ የሚሰጡበት ሂደት ሲሆን ለምርምርም ሆነ ለሌሎች ጉዳዮች ሃሳብና በቂ መረጃን ለማግኘት ጠቀሜታዉ የጎላ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የሚገኘውን መረጃ ከእያንዳንዱ ሰው ተከታትሎ ለመመዝገብና ለማደራጀት አስቸጋሪ ስለሚሆን የተጠኚዎች የናሙና መጠን ማነስ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በዚሁ መሰረት 9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ ሰባት መምህራንና ዘጠኝ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በናሙናነት ተመርጠዉ መረጃ ሰጥተዋል፡፡ ለተሳታፊዎቹ የቀረቡት ቃለ-መጠይቆች ለጥናቱ ጠቃሚ መረጃ ያስገኛሉ ተብለዉ የታመነባቸው ናቸዉ፡፡ ጥያቄዎቹ ልቅ በሆነ አቀራረብ የተዘጋጁ ሲሆን ተሳታፊዎችም የጥናቱ ዓላማ ከተብራራላቸዉ በኋላ ተገቢዉን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

### 3.4.3. የቡድን ተኮር ውይይት

በጥናቱ ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የተመረጡ ተማሪዎችን በስምንት ቡደኖች በማደራጀት የቡድን ተኮር ውይይት ተከናውኗል፡፡ ውይይቱ የተካሄደዉ ከቀን 10/08/2011-17/08/2011 ዓ.ም ድረስ ነዉ፡፡ ይህም አንድ ቡድን በአማካይ ከ6-8 አባላት እንዲኖረዉ በማድረግ ወንዶች 28፣ ሴቶች 27፣ በድምሩ 55 ተማሪዎች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ በመምረጫ መስፈርትነት ስራ ላይ የዋለው በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ከሌሎቹ የተሻለ ግንዛቤ ያላቸዉ እና የፆታ ስብጥርን ያማከለ ነዉ፡፡ በቡድን ተኮር ውይይት ጊዜ በቃለ-መጠይቅና በምልከታ ወቅት በቂ ዉጤት ያልተገኘላቸው መረጃዎችን በቡድን ሆነው እየተወያዩ ማብራሪያ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ለዉይይቱ መሳካት በቅድሚያ ከየክፍሉ የተመረጡ ተማሪዎች በየትኛው ቡድን ውስጥ መሳተፍ እንደሚችሉ ዕጣ እንዲወስዱ ከተደረገ በኋላ መደበኛ ትምህርታቸዉን ሳይነካ ተደራራቢ ያልሆነ ቀንና ሰዓት ወስነዉ ተስማሙ፡፡ የተመረጠውም ሰኞ፣ማክሰኞና ረቡዕ ከሰዓት ስምንት ሰዓት እስከ አስር ሰዓት ነዉ፡፡ የከሰዓት ፈረቃ የተመረጠበት ምክንያት የትምህርት ፈረቃቸው ከጠዋት መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ነዉ፡፡ በዉይይቱ አንዱ ተሳታፊ ብቻዉን ሰፊ ጊዜ በመዉሰድ ሌሎች ተሳታፊዎች ዕድል እንዳይነፈጉ ለማድረግ እያንዳንዱ ተወያይ የሚሰጠዉን አስተያየት ከርዕስ ውጪ ሌሎች ጉዳዮችን ሳያካትት በተወሰነለት ጊዜ እንዲያጠናቅቅ ተደርጓል፡፡ በአጠቃላይ በተመሳሳይ ትምህርት

ቤቶች ያሉ ተሳታፊ ቡድኖች በወይይቱ ወቅት መደራረብ እንዳይፈጥሩ በማድረግ ውይይቱ ተጠናቅቋል፡፡ የቡድን ተኮር ዉይይቱ ዉጤትም ከቃለ-መጠይቅ ጋር እየተመሳከረ ቀርቧል፡፡

## 3.5. የመረጃ ትንተና ስልት

ለዚህ ጥናት ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎች ከክፍል ውስጥ ምልከታ፣ ከቃለ መጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይቶች ተሰባስበው ተደራጅተዋል፡፡ ከቃለ መጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይቶች  የተገኙት ማስረጃዎች ከዚህ ጥናት መሰረታዊ ጥያቄዎች አንፃር በጭብጥ በጭብጥ እንዲደራጁና ተጠቃለው እንዲቀርቡ ተደርገዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አማካኝነት የተሰበሰቡት መረጃዎችን በትንተና ሂደት ለማመሳከር ተሞክሯል፡፡

በአጠቃላይ፣ የመረጃ ዘዴዎችን በማዘጋጀት፣ መረጃዎችን በመሰብሰብና በመተንተን ሂደት የሚፈጠሩ ስህተቶችን ለመቀነስ የተለያዩ ጥረቶች ተከናውነዋል፡፡ ከጥናቱ ጋር ቀጥተኛ ተዛማጅነት ያላቸውን ፅሁፎች በመቃኘት የተገኙትን መረጃዎች በምሳሌ በማስደገፍ በሰንጠረዥ ፣በትንተና እና በገለጻ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ በጥናታዊ ፅሁፉ የተነሱ ጥያቄዎችን ለመመለስና ዓላማዉን ከግብ ለማድረስ የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደየባህሪያቸው በቅደም ተከተል ከተደራጁ በኋላ ተብራርተዉ ቀርበዋል፡፡ በዚሁ መሰረት መረጃዎቹ ገላጭ የአተናተን ዘዴን በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡ በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተገኙ መረጃዎችም ተመሳክረዋል፡፡ እነዚህን ተግባራት በማከናወንም የጥናቱን ግኝቶች መሰረት በማድረግ የተሰጡት ማጠቃለያዎች አግባብነት ያላቸው እንዲሆኑ ጥረት ተደርጓል፡፡

# ምዕራፍ አራት
# የመረጃ ትንትናና የውጤት ማብራሪያ

## 4.1. የመረጃ ትንተና

የዚህ ምዕራፍ ትኩረት የተሰበሰቡ መረጃዎችን ተንትኖ ውጤቱን መግለጽ ሲሆን ሶስት ንዑሳን ክፍሎች አሉት፡፡መጀመሪያ ላይ ከክፍል ዉስጥ ምልከታዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች የተተነተኑበት፣ ሁለተኛ ከመምህራን የተገኙ የቃለ-መጠይቅ ዉጤቶች የተተነተኑበት፣ በመጨረሻም ከተማሪዎች የተገኙ የቡድን ተኮር ዉይይት ዉጤት ከቃለ-መጠይቅ ጋር እየተመሳከረ ቀርቧል፡፡

ጥናቱ ሶስት ዝርዝር አላማዎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ ተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት ያላቸው ግንዛቤን መገምገም፡፡ ሁለተኛዉ በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በተከታታይ ምዘና ለመመዘን የሚጠቀሙዋቸውን ስልቶች መፈተሽ ነዉ፡፡በመጨረሻም በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተከታታይ ምዘናዎችን ሲተገብሩ የሚያጋጥሟቸው ችግሮች መለየት ናቸዉ፡፡ እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የተሰበሰበዉ መረጃ ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም እንደሚከተለዉ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

### 4.1.1. የክፍል ውስጥ ምልከታ መረጃ ዉጤት ትንተና

በጥናቱ መምህራን በሚያስተምሩበት የተለያዩ ክፍሎች አንድ መምህር ለሁለት ጊዜያት በአጠቃላይ ለአስራ አራት ዙር ተከታታይ የክፍል ዉስጥ ምልከታ ተከናውኗል፡፡ የተገኘዉ ዉጤትም ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ** 1፦ከማስተማር ሂደት በፊት የመምህሩን ተግባር በተመለከተ የተገኘ መረጃ

| ተ/ቁ | የመምህሩ ተግባር | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ተከናዉኗል | | አልተከናወነም | |
| 1 | ከማስተማር ሂደት በፊት የመምህሩ ተግባር | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 1.1. | ዋና ርዕስና ንዑሳን ርዕሶችን ማሳወቅ | 14 | 100 | - | - |
| 1.2. | ቅድመ ፈተና መስጠት | 2 | 14.3 | 11 | 85.7 |

ሰንጠረዥ 1 የሚያስረዳዉ ከማስተማር ሂደት በፊት ዋና ርዕስና ንዑሳን ርእሶችን ከማስተዋወቅ አንፃር 14(100%) የምልከታ ክፍለ ጊዜያት የተከናወኑ ሲሆን ለተማሪዎች ቅድመ ፈተና የተሰጠዉ 2(14.3%) የምልከታ ክፍለ ጊዜያት ብቻ መሆኑን ነው፡፡

ይህን አስመልክቶ ዳንኤል (1999፡7) ከማስተማር ሂደት በፊት ተከታታይ ምዘና የሚደረግበት ዋና ዓላማ ተማሪዎች በሂደት ስለሚማሩት ምዕራፍ ዋና ርዕስና ንዑስ ርእሶች ያላቸውን ቅድመ ግንዛቤና ልምድ በተመለከተ መረጃ ለመሰብሰብ፤ ተማሪዎች ስለሚማሩት ይዘት የተዛባ ጽንስ ሐሳብ ካላቸው መረጃ ለመሰብሰብ፤ በመጨረሻም የተገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግ ይመጥናሉ የሚባሉት ተግባራትንና መልመጃዎች ላይ እቅድ ለማቀድ፣ ወዘተ ናቸው፡፡በማለት ያብራራል

ከዚህ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር በምልከታዉ ወቅት ማረጋገጥ የተቻለዉ መምህራን የዕለቱን ትምህርት ከመጀመራቸዉ አስቀድመዉ ተማሪዎች በሂደት ስለሚማሩት ትምህርት ዋና ርዕስና ንዑሳን ርእሶች ያላቸውን ቅድመ ግንዛቤና ልምድ ፣ስለሚማሩት ይዘት የተሳሳተ ጽንስ ሐሳብ ካላቸው ለማየት ሲባል የሚተገበሩ መሆኑን ነዉ፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኛዉ መምህራን በዕለቱ ስለሚያስተምሩት ርዕስ ቀደም ብሎ ለተማሪዎች ቅድመ ፈተና፣ተግባራትንና መልመጃዎችን የማይሰጡ መሆኑን ነዉ፡፡

ይህም መምህራን ለማስተማር በሚያቅዱበት ጊዜ ተማሪዎቻቸዉ ስለሚያስተማሩት ርዕስ ምን ያህል ግንዛቤ እንዳላቸው ትምህርቱን ማስተማር ከመጀመራችን በፊት ለማወቅ እንደሚያስቸግራቸዉ ያሳያል፡፡ ይህንን ሀሳብ በማጠናከር ተስፋ (2000፣27) ከቅድመ ግንዛቤ ፈተና የተገኘው ውጤት አስተማሪው ለወደፊት ለማስተማር የሚጠበቅበትን ትምህርት በአግባቡ እንዲያቅድና የተለያዩ የምዘና ተግባራትን በዕቅዱ ውስጥ እንዲያካትት ዕድል ይፈጥርለታል፡፡ በማለት ይገልፃሉ፡፡

**ሰንጠረዥ** 2፦በመማር ማስተማር ሂደት የመምህሩን ተግባር በተመለከተ የተገኘ መረጃ

| ተ/ቁ | የመምህሩ ተግባር | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ተከናዉኗል | | አልተከናወነም | |
| 2 | በመማር ማስተማር ሂደት የመምህሩ ተግባር | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 2.1. | የክፍል ሥራ ማሰራት | 12 | 85.7 | 2 | 14.3 |
| 2.2. | እየተዘዋወረ ክትትል ማድረግ (የክፍል ውስጥ ምልከታ) | 9 | 64.3 | 5 | 35.7 |
| 2.3. | የጓደኛ ለጓደኛ ምዘና እንዲካሄድ ማድረግ | 2 | 14.3 | 12 | 85.7 |
| 2.4. | ተማሪዎች እየወጡ እንዲያቀርቡ ማድረግ | 4 | 28.6 | 10 | 71.4 |
| 2.5. | ከተማሪዎች ጋር ጥሩ መስተጋብር መፍጠር (የመምህር ተማሪ ውይይት ማካሄድ) | 11 | 78.6 | 3 | 21.4 |
| 2.6. | ተማሪዎች ራሳቸውን እንዲገመግሙ ማድረግ | 1 | 7.2 | 13 | 92.8 |

ሰንጠረዥ 2 የሚያስረዳዉ በመማር ማስተማር ሂደት የመምህሩ ተግባር የክፍል ሥራዎችን ከማሰራት አንፃር 12(85.7%)፣ የተለያዩ የግልና የቡድን ተግባራት ወቅት እየተዘዋወረ ክትትል ማድረግ ደግሞ 9(64.3%) ተከናዉኗል፡፡ ከዚህም ሌላ 2(14.3 %) ጊዜ ብቻ የጓደኛ ለጓደኛ ምዘና እንዲካሄድ ሲደረግ 4(28.6%) ጊዜ ብቻ ተማሪዎች እየወጡ እንዲያቀርቡ ተደርጓል፡፡ መምህራን ከተማሪዎች ጋር

ጥሩ መስተጋብር እንደሚፈጥሩ የታየ ሲሆን ይህም 11 (78.6%) ጊዜያት ነዉ፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎች ራሳቸውን እንዲገማገሙ 1(7.2%) ጊዜ ብቻ ተከናዉኗል፡፡

ይህን አስመልክቶ Capper (1996) ተከታታይ ምዘና ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት ምን ያህል ውጤታማ እንደሆኑ መምህራን ደግሞ የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል ምን ያህል እንደሰሩና ተማሪዎች የራሳቸውን መማር ምን ያህል እንዳሻሻሉ ተደጋጋሚ ምዘና የሚደረግበት ሂደት ነው፡፡ በመሆኑም ተከታታይ ምዘና የተማሪዎችን ተፈላጊውን የመማር ውጤት ምን ያህል እንዳሳኩ ለማረጋጋጥ ተማሪዎች ምን መሻሻል እንዳሳዩ ለማረጋገጥና በመማር ማስተማር ሂደት ላጋጠሙ ችግሮችና እጥረቶች የተወሰዱ እርምጃዎችን ለማረጋገጥ ይረዳሉ፡፡ በማለት ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም ለወደፊት ለማስተማር የሚጠበቅበትን ትምህርት በአግባቡ እንዲያቅድና የተለያዩ የምዘና ተግባራትን በዕቅዱ ውስጥ እንዲያካትት ዕድል ይፈጥርለታል፡፡

ከዚህ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር በምልከታዉ ወቅት ማረጋገጥ የተቻለዉ መምህራን በሚያስተምሩበት ወቅት በብዛት ክፍል ውስጥ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን፣የክፍል ሥራ፣ ከተማሪዎች ጋር ጥሩ መስተጋብር በመፍጠር በክፍል ውስጥ የሚሰሩትንና የሚናገሩትን በመከታተል በመምህርና በተማሪ መካከል የሚካሄዱ ውይይት መደረጉን ነዉ፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኛዉ መምህራን ተማሪዎች ራሳቸውን በራሳቸው የሚመዝኑበት ሂደትና ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ሥራዎቻቸውን እርስ በርሳቸው የሚመዘኑበት ስልት ከጥቂት መምህራን በስተቀር እየተተገበረ እንዳልሆነ ነዉ፡፡ በአጠቃላይ መምህራን በአማርኛ ቋንቋ ክፍል ውስጥ የተማሪዎችን የተለያዩ የክፍል ውስጥ ተግባራትን እየወጡ እንዲያቀርቡ ቢያደርጉ የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታና ፍላጎት መመዘን ይችላሉ፡፡ ይህም መምህራን ለማስተማር በሚያቅዱበት ጊዜ በተማሪዎች ላይ ስለሚታዩ ባህሪያትና ስለአጠቃላይ የመማሪያ ክፍል ሁኔታን አስመልክቶ ተከታታይነት ባለው ሂደት መረጃ ለመሰብሰብ እንደሚረዳቸዉ መረዳት ይቻላል፡፡

ይህንን ሀሳብ በማጠናከር ዳንኤል (1999፣7) በመማር ማስተማር ሂደት ሂደታዊ ተከታታይ ምዘና የሚተገበርበት ዋና ዓላማ ተማሪዎች የሚማሩት ትምህርት ምን ያህል እየተከታተሉ ናቸው? ምን ያህል እየተረዱ ናቸው? ከተማሩት ውስጥ ምን ያህሉን ተገንዝበዋል? ምን ዓይነት ችግር አጋጥሟቸዋል? ወዘተ በሚሉ ጉዳዮች ዙሪያ መረጃ ለመሰብሰብ፣ በደንብ እየተከታተሉ ያሉትን ለማበረታታት፣ የመማር ችግር ያጋጠማቸውን እንደ ችግራቸው መጠን የተለያዩ ድጋፎችን ለመስጠት፣ በማስተማር ሂደቱ ላይ መሻሻል በሚገባቸው ነጥቦች ዙሪያ ማስተካከያ ለማድረግ ከትምህርት ዕቅድ ጀምሮ እስከ ድጋሚ ማስተማር ሊያጠቃልል ይችላል፡፡

**ሰንጠረዥ 3፦የተከታተይ ምዘና ዘዴዎች መጠቀምን በተመለከተ የተገኘ መረጃ**

| ተ/ቁ | የመምህሩ ተግባር | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ተከናዉኗል | | አልተከናወነም | |
| 3 | የተከታተይ ምዘና ዘዴዎችን መጠቀም | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 3.1. | የቃል ጥያቄ ማካሄድ | 14 | 100 | - | - |
| 3.2. | የቤት ሥራ መስጠት | 13 | 92.8 | 1 | 7.2 |
| 3.3. | የቡድን ተግባራትን ማሰራት | 7 | 50 | 7 | 50 |
| 3.4. | የግል ሥራን ማሰራት | 12 | 85.7 | 2 | 14.3 |
| 3.5. | ሙከራና ፈተና መስጠት | 1 | 7.2 | 13 | 92.8 |
| 3.6. | ሰነደ ትምህርት መጠቀም | - | - | 14 | 100 |

ሰንጠረዥ 3 የሚያስረዳዉ መምህሩ የተከታተይ ምዘና ዘዴዎችን ከመጠቀም አንፃር የቃል ጥያቄ 14(100%)፣ የቤት ሥራ 13(92.8%) ጊዜ መሰጠቱን ለመታዘብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም 7(50%) መምህራን የቡድን ተግባራትን ማሰራታቸዉን ለመመልከት ሲቻል የግል ሥራዎች 12(85.7%) ጊዜ መሰጠታቸዉን ታይቷል፡፡ ይሁን እንጂ ከ 1(7.2%) ክፍለ ጊዜ በስተቀር መምህራን ሙከራና ፈተና መስጠት እንዲሁም ሰነደ ትምህርት ሲጠቀሙ አልተስተዋለም፡፡

ይህን አስመልክቶ ዳንኤል (1999፡7) መምህራን ሊጠቀሙባቸው ከሚችሉ የአጠቃላይ ተከታታይ ምዘና ዘዴዎች ውስጥ በሥርዓተ ትምህርት ማቴሪያሉ ላይ የተመሠረቱና የተካተቱ ሙከራዎች፣ ከትምህርቱ ዓላማዎች ጋር የተዛመደ በመምህራን የተዘጋጁ ሙከራዎች፣ ከትምህርቱ ዓላማዎች ጋር የተዛመዱ በሥርዓት የታረሙ ፕሮጀክቶች፣ በተማሪ የተሰሩ የተግባር ውጤትና ተማሪዎች ተግባሩን ሲያከናውኑ የሚደረግ ምዘና፣ ከትምህርቱ ዓላማዎች ጋር የተዛመደ በሴሚስተሩ ወይም በዓመቱ መጨረሻ ላይ የሚከናወን ምዘና፡፡

ይህም ከማስተማር በኃላ ተከታታይ ምዘና የሚካሄድበት ዋና ዓላማ በየምእራፉ የተካተቱትን የትምህርት ዓላማዎች መሰረት ባደረገ መልኩ ተማሪዎች ምን ያህል የባህርይ ለውጥ አምጥተዋል? በሚሉ ጥያቄዎች ዙሪያ መረጃ ለመሰብሰብ፡፡ በተሰበሰበው መረጃ መሰረት አንድ ተማሪ አልፏል ወይስ ከሚጠበቀው በታች አምጥተዋል ብሎ ለመወሰንና ውጤት ለመስጠት እንዲሁም ከተፈለገው በታች ያመጡትን ተማሪዎች በድጋሚ ለማዘጋጀት ይውላል፡፡

ከዚህ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር በምልከታዉ ወቅት ማረጋገጥ የተቻለዉ መምህራን የተከታተይ ምዘና ዘዴዎችን ከመጠቀም አንፃር ሁሉም የቃል ጥያቄ፣የቤት ሥራ፣የግል ሥራን በማሰራት ተማሪዎች የተማሩትን ምን ያህል እንደተገነዘቡትና ተማሪዎች የት ላይ ችግር እንዳለባቸው ለማወቅ እየተጠቀሙበት መሆኑን ሲሆን ምን ያህል የተማሩትን ትምህርት እየተከታተሉ እንደሆነ የሚያረጋግጥቡት መሆኑን ነዉ፡፡ ይሁን እንጂ በክፍል ዉስጥ ምልከታዎች ወቅት በግልም ሆነ በቡድን የሚሰሩ የተለያዩ ስራዎችን እንዲያከናውኑ ቢደረግም ሰነደ ትምህርት እየተተገበረ አለመሆኑን ነዉ፡፡

ይህንን ሀሳብ በማጠናከር Hamis (1997) “ተከታታይ ምዘና ግልፅ የሆነ እቅድ ያለው ሆኖ መምህራን የተማሪዎችን ችሎታ የሚገመግሙባቸውን የተከታታይ ምዘና መሳሪያዎች የሚይዝ እንዲሁም ግምገማዎች የሚደረጉባቸውን ጊዜያት ስርዓትን ተከትለው ተከታታይነት ባለው መልኩ የሚቀርቡበትና ዕቅድ በሚዘጋጅበት ጊዜ ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ነገሮች ምዘናው የሚካሄድበት ስልት፣ ጊዜ፣ የሚተኮርባቸው የትምህርት ክፍሎች፣ የውጤት አያያዝ

ወዘተ መሰረት አድርጎ መሆን አለበት፡፡" በማለት ያብራራል፡፡ በመሆኑም ለወደፊት ለማስተማር የሚጠበቅበትን ትምህርት በአግባቡ እንዲያቅድና የተለያዩ የምዘና ተግባራትን በዕቅዱ ውስጥ እንዲያካትት ዕድል ይፈጥርለታል፡፡

**ሰንጠረዥ 4፦ምጋቤ ምላሽ (አስተያየት) መስጠትን በተመለከተ የተገኘ መረጃ**

| ተ/ቁ | የመምህሩ ተግባር | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ተከናዉኗል | | አልተከናወነም | |
| 4 | ምጋቤ ምላሽ (አስተያየት) መስጠት | በቁጥር | % | በቁጥር | % |
| 4.1. | ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ መስጠት | 13 | 92.8 | 1 | 7.2 |
| 4.2. | ጽሑፋዊ ምላሽ መስጠት | 3 | 21.4 | 11 | 78.57 |

ሰንጠረዥ 4 የሚያስረዳዉ መምህሩ ምጋቤ ምላሽ (አስተያየት) ከመስጠት አንፃር 13(92.8%) ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ የተሰጠ ሲሆን ጽሑፋዊ ምላሽ ደግሞ ለ 3(21.4%) ክፍለ ገዜያት ብቻ መሰጠቱን ለመመልከት ተችሏል፡፡

ይህን አስመልክቶ Nitko (2008) መምህራን ተማሪዎች በመማር ሂደት የሚያከናውኗቸውን ተግባራት፣ የሠሯቸውን ሥራዎች እና የሰጡትን መልስ በመመርመርና በመተንተን ያገኙትን ለተማሪዎች መልሰው የሚያሳውቁበት መንገድ ተማሪዎች አፈፃፀማቸውን ወይም ክንዋኔያቸውን እንዲያውቁ ይረዳቸዋል፡፡ ይህም ተማሪው እንዴት እንደሚሻሻል የሚደረግለት ድጋፍ የያዘ ሲሆን ጥንካሬን፣ መሻሻልን የሚፈለገውንና የማሻሻያውን ዘዴ የሚያሳይ ነው፡፡

ከዚህ ፅንሰ ሀሳብ አንፃር በምልከታዉ ወቅት ማረጋገጥ የተቻለዉ መምህራን የተማሪዎችን ተሳትፎ በመከታተል አብዛኛዉ ጊዜ ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ተማሪዎችን ለማነቃቃትና ተማሪዎች የራሳቸውን ትምህርት እንዲያጎለብቱ ለማስቻል የሰጡትን መልስ በመመርመር ለተማሪዎች መልሰው የሚያሳውቁበት መንገድ ቢኖርም ጽሑፋዊ ምላሽ የማይሰጡ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

## 4.1.2. የመምህራን ቃለ-መጠይቅ መረጃ ዉጤት ትንተና

በጥናቱ የመምህራን ቃለ-መጠይቅ ተግባራዊ የሆነው ከቀን 23/07/2011-26/07/2011 ዓ.ም ድረስ ሲሆን በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች በ2011 ዓ.ም የአማርኛ ቋንቋን በማስተማር ላይ የሚገኙ ሰባት መምህራን የሰጧቸው ምላሾች አንድ ላይ ተጨምቀዉ ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

1. ተከታታይ ምዘና ለእርሶ ምን ማለት ነዉ? ለሚለዉ ጥያቄ የተሰጡ ምላሾች፡-

- *"በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ተከታታይ በሆነ ድርጊት የተማሪዎችን የመማር ተነሳሽነት የሚያጎለብትናተማሪዎች በተለያዩ ተግባራት እንዲሳተፉ በማድረግ ብቁ የሆነ ትዉልድ ለመቅረፅ የሚጠቅም ነዉ (መላሽ ኮድ 01)፡፡*

- *"ተማሪው በዕውቀት በአስተሳሰብና በክህሎት ያገኘውን ለውጥ በየጊዜው ተከታትሎ ለማሳየት የሚረዳ ስልት ሲሆን ተማሪዎች በሚያውቁትና ሊያውቁት በሚፈለገው መካከል ያለውን የእውቀት ክፍተት ለመቀነስ የሚደረግና የእውቀት ክፍተቱን አስመልክቶ መረጃ ለማግኘት የሚደረግ ሂደት ነው (መላሽ ኮድ 02፣03፣05)፡፡*

- *"በብዛት ትግበራ ላይ የሚዉል ድርጊት ሲሆን ይሄዉም በቤት ሥራ፣ በግል ሥራ፣ በቡድን ስራዎች፣ በራስ ምዘና የተማሪውን ብቻ ሳይሆን የመምህሩን የማስተማር ስልት፣ዝግጅትና ዕውቀት ከሚገኘው ለማሻሻል የሚያግዝ ነው፡፡ መምህራን ተማሪዎችን ለመመዘን የሚያከናውኗቸው የተለያዩ ተግባራት ሲሆኑ የተገኘውንም መረጃ የመማር ማስተማሩን ተግባራት በሂደት የማሻሻልና የተማሪዎችን ፍላጎት ለሟሟላት የሚረዳ ነዉ፡፡"(መላሽ ኮድ 04፣06፣07)፡፡*

2. ከተከታታይ ምዘና ጋር በተያያዘ ስልጠና ተሳትፈው ያውቃሉ? መልስዎ አዎ ከሆነ የሥልጠናዉ ይዘቶች ምን ምን ነበሩ? ስልጠናዉ በቂ ነበር ብለዉ ያስባሉ? ለሚለዉ ጥያቄ የተሰጡ ምላሾች፡-

- *"በጥናቱ ተተኳሪ ከሆኑ መምህራን አራት መምህራን ብቻ ከተከታታይ ምዘና ጋር በተያያዘ ስልጠና መሳተፋቸዉን ገልፀዋል፡፡ቀሪዎቹ ሶስት መምህራን ደግሞ ከተከታታይ ምዘና ጋር በተያያዘ ስልጠና ተሳትፈን አናዉቅም፡፡"*

  *(መላሽ ኮድ 03፣04፣05፣06)፡፡*

ከተከታታይ ምዘና ጋር በተያያዘ ስልጠና መሳተፋቸዉን የገለፁ መምህራን የሥልጠና ይዘቶችን ሲያብራሩ፡

- *"ስልጠናዉ በተከታታይ ምዘና ሂደት ዕቅድ ማውጣት የመጀመሪያ ተግባር መሆኑንና የተለያዩ የምዘና ዘዴዎችን በተከታታይ ምዘና ዕቅድ ውስጥ ማካተት በራሱ በቂ እንዳልሆነ፣ ስለ የተከታታይ ምዘና ፎርም፣ የጥያቄ አወጣጥና የፈተና ስርዓት፣ የተከታታይ ምዘና ሂደት፣ አገባብና ጥቅም፣ ተከታታይ ምዘና እንዴትና መቼ መሰጠት እንዳለበት፣ ስለ የክትትል መዝገብ ምንነትና አሰራር፣ ስርዓተ ትምህርት ተኮር ምዘና፣ የተማሪዎችን የዕውቀት የክህሎትና የዝንባሌ ዝርዝር ባህሪያት መግለጫ እንዴት ማደራጀት እንደሚቻል የተማሪዎችን ሰብዓዊ ባህሪያትና ግለሰባዊ ገፅታዎችን ለመመዘን እንዳለብን ሰልጥነናል፡፡" (መላሽ ኮድ 03፣04፣05፣06)*

3. የተከታታይ ምዘናው ሥልጠና በተከታታይ ምዘና አተገባበርዎ ላይ ያመጣው ለውጥ ካለ ሀሳብዎን ቢገልፁልኝ? ለሚለዉ ጥያቄ የተሰጡ ምላሾች፡-

በስልጠናዉ መሳተፋቸዉን የገለፁ መምህራን ሥልጠናዉ በአተገባበራቸዉ ላይ ያመጣውን ለውጥ ሲያብራሩ፡

- *"ተማሪዎች በምን ደረጃ እንዳሉና ጠንካራና ደካማ ተማሪዎችን ለይቶ ድጋፍ ለመስጠት አስችሎኛል፡፡ የተማሪዎችን አጠቃላይ ዕውቀት ክህሎት አመለካከት የትምህርት አቀባበልና አካሄድ በመመዘን ተማሪዎችን ለማገዝ እንዲሁም በተማሪዎች፣ በመምህራንና በትምህርት ቤቱ ላይ ጠቃሚ ውሳኔ ለመስጠት መረጃ የሚሰበሰብበት የምዘና ሰርዓት መሆኑን ተረድቻለሁ፡፡ ጠንካራና ደካማ ተማሪዎችን ለመለየት አስችሎኛል፣ በክፍል ውስጥም ሆነ*

*ከክፍል ዉጭ ችግሮችን መፍትሄ ለመስጠት አስችሎኛል፡፡" (መላሽ ኮድ 03፣04)፡፡*

ከዚህም ሌላ ሁለቱ መምህራን የተለየ ሀሳብ አቅርበዋል፡፡

- *"ይህን ያህል ለውጥ አምጥቷል ብለን አናስብም ምክንያቱም በክፍል ዉስጥ ለመተግበር ያስቸግራል ይህም ተማሪዎች ውጤታማ፣ ቀልጣፋና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ለመመዘን ብዙ ተማሪዎች ባሉበት የመማሪያ ክፍል ውስጥ አስተማማኝነት ያለው ምዘና ተግባራዊ ማድረግ አስቸጋሪ ነው፡፡"(መላሽ ኮድ 05፣06)፡፡*

4. የተከታታይ ምዘናን እንዴት ይተገብራሉ? የሚተገብሩት የምዘና ዓይነት የትኛዉ ነዉ? ለሚለዉ ጥያቄ የተሰጡ ምላሾች፦

- *"በመጀመሪያ ደረጃ ዓመታዊ ዕቅዳችን ላይ አካተን ለት/ቤቱ እናስገባለን፡፡ በማስከተልም ዓመታዊ ዕቅዱ ላይ በመመርኮዝ ሳምንታዊና ዕለታዊ እቅድ ላይ ክፍል ዉስጥ በምንገባበት ጊዜ ምን ምን ተግባራትን እንደምናከናዉን በማቀድ እንዘጋጃለን፡፡ ለማስተማር እንደገባን የዕለቱን ትምህርት ከመጀመራችን በፊት ተማሪዎች በሂደት ስለሚማሩት የዕለቱ ትምህርት ዋና ርዕስና ንዑሳን ርዕሶች ያላቸውን ቅድመ ግንዛቤና ልምድ ለማየት ሲባል እናስተዋዉቃለን፡፡" (መላሽ ኮድ 03፣04፣05፣06፣07)፡፡*

ሁለቱ መምህራን ብቻ ሲገልፁ፣

- *"ተማሪዎች ስለሚያስተምሩት ርዕስ ምን ያህል ግንዛቤ እንዳላቸው ለማወቅ ቅድመ ፈተና፣ተግባራትንና መልመጃዎችን እንሰጣለን፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የምንጠቀምበት ስልቶች የክፍል ስራ፣ እየወጡ ማቅረብ፣ የቃል ጥያቄዎችና የቤት ስራ በተደጋጋሚ እንሰጣለን፡፡ የግል ስራ፣ የቡድን ስራ፣ የመምህር ተማሪ ውይይት፣ አሳታፊ የመማር ማስተማር ሥነ ዘዴዎች፣ የአቻ ለአቻ እና ግለ ግምገማ በተወሰነ ጊዜ የተማሪ ብቃት ላይ ዳኝነት ለመስጠት እንጠቀምበታለን፡፡" (መላሽ ኮድ 01፣02)፡፡*

5. በተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች (ደካማ-ጎኖች) ካሉ? የተገኙ ዉጤቶች (ጠንካራ-ጎኖች) ካሉ? ለሚለዉ ጥያቄ የተሰጡ ምላሾች፡-

በተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት ያጋጠሟቸውን ችግሮች ሲገልጹ፡-

- *“ብዙ ተማሪዎች በአንድ ክፍል ውስጥ በመገኘታቸዉ በትክክል ለመተግበር ከባድ የስራ ጫና ፈጥሮብናል፡፡ ተማሪዎች በብዛት ከትምህርት ቤት በሚቀሩበት ጊዜ የተከታታይ ምዘናን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ያስቸግራል፡፡ የክፍለ ጊዜ ብዛት ትግበራዉ ላይ መሰልቸት አስከትሏል፡፡ተጨማሪ ድጋፍና ስልጠና አለማግኘት ለዘብተኛ እንድንሆን አድርጎናል፡፡ በትምህርት ቤት የእርስ በእርስ ግምገማ ስርዓት አለመዘርጋት አንዱ መምህር ከሌላኛዉ እንዳይማር አድርጓል፡፡" (መላሽ ኮድ 01፣02.03)፡፡*

- *"ተማሪዎች በጓደኞቻቸው ሥራዎች ላይ ብቻ ጥገኛ እንዲሆኑ ስለሚያደርግ የራሳቸውን ስራ በራሳቸው መገምገምን እንዳይለማመዱ አድርጓል፡፡"(መላሽ ኮድ 04)፡፡*

- *"ለቡድን ሥራ ተሳታፊዎች አንድ ዓይነት ውጤት ስለሚሰጥ በቡድኑ ውስጥ ያለውን/ችውን የእያንዳንዱን/ዋን ተማሪ ሥራ ምዘና በችሎታው/ዋ መሠረት እንዳይሆን በማድረግ እውነታውን ያዛባዋል፡፡ ለመማር አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን በመዳሰስ ፈንታ አብዛኞቹ መምህራን ለመመዘን ቀላል በሆኑ ነገሮች ላይ ብቻ ያተኩራሉ፡፡" (መላሽ ኮድ 05፣06፣07)፡፡*

በተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት ዉጤቶች (ጠንካራ-ጎኖች) ሲገልጹ፡-

- *"የተማሪዎችን የመማር ዝግጁነት፣ ውጤትና ባህሪያት ለመለካት አስችሎናል፡፡ የተማሪዎችን ጠንካራና ደካማ ተማሪዎችን በመለየት መፍትሄ ለመስጠት፡፡ የተማሪዎችን የትምህርት ውጤትና የባህሪ ለውጥ ለማሻሻል ያስችላል።"(መላሽ ኮድ 01፣02፣03)፡፡*

- *"የትምህርት ዕቅድን ለመከለስና የማስተማር ዘዴን ለማሻሻል፡፡ ለደካማ ተማሪዎች የምክርና የአመራር አገልግሎት በመስጠት የተማሪዎችን የመማር ዕድገትና ለውጥ ለወላጆች መረጃ ለመስጠት፡፡"(መላሽ ኮድ 04፣05)፡፡*

- *"ተማሪዎችን እንደ የቋንቋ ችሎታቸው በመለየት በክፍል ውስጥ የተማሪዎችን ቁጥጥርና ክትትል ለማድረግ፡፡ በዓመታዊ ዕቅዳችን ላይ የታቀዱ ግቦች በሚገባ መሳካትና አለማሳካታቸዉን ለማረጋገጥ፡፡ በክፍል ውስጥ አሳታፊ መማር ማስተማር ተግባራዊ እንዲሆንና ጾታዊ ተሳትፎ ለማረጋገጥ፡፡"(መላሽ ኮድ 06፣07)፡፡*

6. በትምህርት ቤታችሁ የተከታታይ ምዘና አተገባበር የተቀመጠውን ግብና ዓላማ ከማሳካትና የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ከማርካት አንጻር ምን ይመስላል? ለሚለዉ ጥያቄ የተሰጡ ምላሾች፡-

- *"መምህራን ጥቅሙን ጠንቅቀው ቢረዱትም በዓላማው ላይ ግን ልዩነት አላቸው፡፡ ይህም ከተማሪ ክፍል ዉስጥ መብዛትም ሆነ ከስራ ጫና የተነሳ የሚተገበረው ምዘና በዓመታዊና ሳምንታዊ ዕቅዶች ላይ ቢኖርም መመህራን የመማር ማስተማር አካል አድርገዉ ባለ መቁጠራቸዉ ትኩረታቸዉ በውጤት እንጂ በሂደት ላይ አይደለም፡፡"*
*(መላሽ ኮድ 01፣02፣03፣04)፡፡*

- *"በትምህርት ቤታችን ጅምሮች ቢኖሩ እንኳ የተዘረጋ የአተገባበር ስልት ባለመኖሩ ግብና ዓላማዉን አሳክቷል ለማለት ያስቸግራል፡፡ ለአብነትም የተከታታይ ምዘና ተግባራት ለመከታተል የሚጠቀሙበት ቅጽ ትምህርት ቤቱ አዘጋጅቶ ቢሰጥም በአግባቡ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል አይደለም፡፡"*
*(መላሽ ኮድ 05፣06፣07)፡፡*

### 4.1.3. የተማሪዎች ቃለ-መጠይቅና የቡድን ተኮር ውይይት ትንተና

በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች በ2011 ዓ.ም 9ኛ ክፍል በመማር ላይ የሚገኙ ተማሪዎች የሰጧቸው ምላሾች የቡድን ተኮር ዉይይቱ ዉጤት ከቃለ-መጠይቅ ጋር እየተመሳከረ ቀርቧል፡፡

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ የዕለቱን ትምህርት ከማስተማራቸዉ በፊት ስለሚያስተምሩት ትምህርት ዋና ርዕስና ንዑሳን ርዕሶችን ያስተዋዉቃሉ? ለሚለዉ ጥያቄ የተሰጡ ምላሾች፦

- *"ሰባት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራቸዉ የዕለቱን ትምህርት ከማስተማራቸዉ በፊት ስለሚያስተምሩት ትምህርት ዋና ርዕስና ንዑስ ርእሶች እንደሚያስተዋዉቁ አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ መምህራን የዕለቱን ትምህርት ማስተማር ከመጀመራቸዉ በፊት አስቀድመዉ በሂደት ስለምንማረዉ ትምህርት ዋና ርዕስና ንዑስ ርእሶች ያለንን ቅድመ ግንዛቤ ይጨምራል፡፡" (ገቺ፣ ቦረቻ እና 1 የእንግቢ ትምህርት ቤት ተማሪ)*
- *"ሁለት ተማሪዎች የተሳሳተ ጽንስ ሐሳብ እንዳይኖረን ለማየት ሲባል እየተገበሩት እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል፡፡በተጨማሪም እንደገለፁት መምህራን በዕለቱ ስለምንማረዉ ርዕስ ምን ያህል ግንዛቤ እንዳለን ለማወቅ ከተወሰነ ጊዜ ቀደም ብሎ ቅድመ ፈተና፣ተግባራትንና መልመጃዎችን ይሰጡናል፡፡"(የእንግቢ ትምህርት ቤት ተማሪዎች)*

ይህንን ሀሳብ የበለጠ ለመረዳት ሲባል በቡድን ተኮር ውይይት የተሳተፉ ተማሪዎች ማብራሪያ እንዲሰጡበት በማድረግ ተጨማሪ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

- *"የዕለቱን ትምህርት ማስተማር ከመጀመራቸዉ በፊት በሂደት ስለምንማረዉ የዕለቱ ትምህርት ዋና ርዕስና ንዑሳን ርዕሶች ያስተዋዉቃሉ፡፡ ነገር ግን መምህራን ቅድመ ተግባራትን አይሰጡም፡፡" (ቡድን 1፣ቡድን 2)*
- *"በሚያስተምሩበት ወቅት የመማር ማስተማር ሂደት ዉስጥ ሂደታዊ ምዘናን የሚተገብሩ ሲሆን አልፎ አልፎ ደግሞ የቡድ ስራዎች፣ ማጠቃለያ*

*ፈተናና ሙከራ አንዱ ምዕራፍ ሲያልቅ፣ በሴሚስተሩ ወይም በዓመቱ መጨረሻ ላይ ይሰጡናል።" (ቡድን 3፣ቡድን 4፣ ቡድን 5)*

- *"ብዙ ጊዜ የክፍል ስራ፣ ከተማሪ ፊት እየወጡ ማቅረብ፣ የቃል ጥያቄዎች፣ የቤት ስራ፣ የግል ስራ፣ የቡድን ስራ፣ የመምህር ተማሪ ውይይት፣ የአቻ ለአቻ እና ግለ ግምገማ በማካሄድ፣ በተገቢ ነጥቦች ላይ ግብረ-መልስ በመስጠት ይተገበራሉ። ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ብቻ እንጂ ጽሑፋዊ ምላሽ የማይሰጡ መሆኑን ነዉ።" (ቡድን 6፣ ቡድን 7፣ቡድን 8)*

2. የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ በክፍል ዉስጥ ምን ዓይነት የምዘና ስልቶችን ይጠቀማሉ? ለሚለዉ ጥያቄ የተሰጡ ምላሾች፡-

- *"ሰባት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራቸዉ የተከታታይ ምዘና ይተገበራሉ በማለት አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል። ሁለት ተማሪዎች ግን የአማርኛ ቋንቋ መምህራቸዉ የተከታታይ ምዘና አልፎ አልፎ ብቻ ነዉ የሚተገብሩት በማለት አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል።(ገቺ፣ ቦረቻ እና 1 የእንግቢ ትምህርት ቤት ተማሪ)*

- *"በየዕለቱ በሚያደርጉት የመማር ማስተማር ሂደት ዉስጥ ሂደታዊ ምዘናን የሚተገብሩ ሲሆን አጠቃለይ ምዘናን ደግሞ የቡድን ስራዎች፣ ማጠቃለያ ፈተናና ሙከራዎችን አንዱ ምዕራፍ ሲያልቅ፣ መንፈቀ ዓመት ወይም በዓመቱ መጨረሻ ላይ ይሰጡናል። አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሙትም የክፍል ስራ፣ ከተማሪ ፊት እየወጡ ማቅረብ፣ የቃል ጥያቄዎች፣ የቤት ስራ፣ የግል ስራ፣ የቡድን ስራ፣ የመምህር ተማሪ ውይይት፣ አሳታፊ የመማር ማስተማር ሥነ ዘዴዎች፣ የአቻ ለአቻ እና ግለ ግምገማ በማካሄድ፣ በተገቢ ነጥቦች ላይ ግብረ-መልስ በመስጠት ይተገበራሉ። ይሁን እንጂ ከቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ያለፈ ጽሑፋዊ ምላሽ የማይሰጡ መሆኑን ነዉ።"(ገቺ፣ እና የእንግቢ ትምህርት ቤት)*

ይህንን ሀሳብ የበለጠ ለመረዳት ሲባል በቡድን ተኮር ውይይት የተሳተፉ ተማሪዎች ማብራሪያ እንዲሰጡበት በማድረግ ተጨማሪ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

- *"በየዕለቱ በሚያደርጉት የመማር ማስተማር ሂደት ዉስጥ ሂደታዊ ምዘናን የሚተገብሩ ሲሆን አጠቃለይ ምዘናን ደግሞ ሙከራዎች፣ የቡድን ሥራዎች፣ ማጠቃለያ ፈተናና ቴስቶችን አንዱ ምዕራፍ ሲያልቅ፣ በመንፈቀ ዓመቱ ወይም በዓመቱ መጨረሻ ላይ ይሰጡናል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠቀሙትም የክፍል ስራ፣ ከተማሪ ፊት እየወጡ ማቅረብ፣ የቃል ጥያቄዎች፣ የቤት ስራ፣ የግል ስራ፣ የመምህር ተማሪ ውይይት፣ አሳታፊ የመማር ማስተማር ሥነ ዘዴዎች፣ የአቻ ለአቻ እና ግለ ግምገማ በማካሄድ፣ በተገቢ ነጥቦች ላይ ግብረ-መልስ በመስጠት ይተገብራሉ፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኛዉ ጊዜ ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ብቻ እንጂ ጽሑፋዊ ምላሽ የማይሰጡ መሆኑን ነዉ፡፡" (ቡድን 6፣ ቡድን 7፣ቡድን 8)*

3. የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ በሚያስተምሩበት ጊዜ ክፍል ዉስጥ እየተዘዋወሩ ክትትል ያደርጋሉ? ለሚለዉ ጥያቄ የተሰጡ ምላሾች፡-

- *"ስድስት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራቸዉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራቸዉ በሚያስተምሩበት ጊዜ ክፍል ዉስጥ እየተዘዋወሩ ክትትል ያደርጋሉ በማለት አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ሶስቱ ተማሪዎች ግን እየተዘዋወሩ ክትትል አያደርጉም በማለት አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡(ቦረቻ እና የእንግቢ ትምህርት ቤት)*
- *"መምህራን እያስተማሩን ያለዉን ትምህርት ምን ያህል እየተከታተልን እንደሆነና ምን ያህል እየተረዳን እንዳለን በብዛት ክፍል ውስጥ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን በመስጠት የክፍል ሥራዎችን እየሰጡና ጥሩ መስተጋብር በመፍጠር ምን ዓይነት ችግር እንዳጋጠመን እየተዘዋወሩ ክትትል ያደርጋሉ፡፡ ከዚህም ሌላ በደንብ እየተከታተልን ከሆነ ጎበዝ እያሉ ያበረታቱናል፣ ችግር ያጋጠማቸውን ደግሞ የተለያዩ ድጋፎችን በመስጠት ዕረፍት ከፈለገ ወጣ ብሎ*

*እንዲመለስ በመፍቀድ ይተገብራሉ፡፡" በማለት አብራርተዋል(ገቺ እና እንግቢ ትምህርት ቤት)*

4. የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ የተለያዩ የግልና የቡድን ተግባራትን ይሰጣሉ? የተሰሩትን የግልና የቤት ስራዎች ያርማሉ? ለሚለዉ ጥያቄ የተሰጡ ምላሾች፦

- *"ሁሉም ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራቸዉ የግል ተግባራትን ይሰጣሉ በማለት አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ አምስት ተማሪዎች ብቻ የቡድን ተግባራትን ይሰጣሉ በማለት አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡" (ገቺ፣ ቦረቻ እና እንግቢ ትምህርት)*

ከዚህ ጋር በተያያዘ ተማሪዎቹ ሲያብራሩ፦

- *"አብዛኛውን ጊዜ መምህራን የክፍል ስራ፣ የቃል ጥያቄዎችና የቤት ስራ በተደጋጋሚ ቢሰጡም የቡድን ስራ ለይ ግን ችግሮች እንዳሉ ጠቁመዋል፡፡ ይሄዉም ተማሪዎች አንዱ ከሌላኛዉ ሀሳብ በመሰራረቅ የጎበዝ ተማሪዎች ጥገኛ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ የተማሪዎችን ተሳትፎ በመከታተል አብዛኛዉ ጊዜ በማረም ምን ያህል ውጤት መያዝ እንዳለባቸው አልፎ አልፎ ተወያይተን ብቻ እንወስናለን፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኛዉ መምህራን እርስ በራሳችን እንድንገማገም አያደርጉም፡፡"(ገቺ፣ ቦረቻ እና እንግቢ ትምህርት)*

ይህንን ሀሳብ የበለጠ ለመረዳት ሲባል በቡድን ተኮር ውይይት የተሳተፉ ተማሪዎች ማብራሪያ እንዲሰጡበት በማድረግ ተጨማሪ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

- *"አዎን አብዛኛዉ መምህራን ያርማሉ፡፡ ይህም አብዛኛውን ጊዜ መምህራን የክፍል ስራ፣ የቃል ጥያቄዎችና የቤት ስራ በተደጋጋሚ ቢሰጡም የቡድን ስራ ለይ ግን የተማሪዎችን ተሳትፎ በመከታተል አብዛኛዉ ጊዜ ያርሙና ምን ያህል ውጤት መያዝ እንዳለባቸው አልፎ አልፎ ተወያይተን ብቻ እንወስናለን፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኛዉ መምህራን እርስ በራሳችን እንድንገማገም አያደርጉም፡፡" (ቡድን 1፣ቡድን 2፣ ቡድን 3)*

5. የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ በተለያዩ ጊዜያት የሚሰጧቸዉ የቤት ስራዎችና የቡድን ስራዎች የአማርኛ ቋንቋ ችሎታህ/ሽን የተሻለ አድርገዋል ብለህ/ሽ ታስባለህ/ሽ? ለሚለዉ ጥያቄ የተሰጡ ምላሾች፡-

- *"አምስት ተማሪዎች አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ ቀሪዎቹ ግን አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ መምህራን የሚሰጧቸዉ የቤት ስራዎች፣ የቡድንና የግል ስራዎችን ጠቀሜታ ሲገልፁ፣(ገቺ፣ ቦረቻ እና 1 የእንግቢ ትምህርት ቤት ተማሪ)*

- *"የመማር ዝግጁነት እንዲኖረኝ አድርገዋል፡፡ ጠንካራና ደካማ ጎኔን ለመለየት፡፡ በአእምሮአዊ ክህሎት ላይ ብቻ ሳይሆን እውቀትንና ክህሎትን እንዲሁም አመለካከትን ፣ስሜትን፣ ዝንባሌንና እምነትን ለመመዘንና ለመለየት፡፡ በየትኞቹ ምዕራፎች ጠንካራ እንደሆኑ በየትኞቹ ደግሞ ድክመት እንዳሳየዉ ለመለየትና ድክመት ባሳየሁበት የትኩረት አቅጣጫ እንድንቀይስ፡፡ የተለያዩ ተግባራትን እየወጣን በምናቀርብበት ጊዜ የቋንቋ ችሎታ፣ ፍላጎት፣ የሀሳብ አደረጃጀትና ችሎታ እንዲኖረን፡፡"(የእንግቢ ትምህርት ቤት ተማሪ)*

ይህንን ሀሳብ የበለጠ ለመረዳት ሲባል በቡድን ተኮር ውይይት የተሳተፉ ተማሪዎች ማብራሪያ እንዲሰጡበት በማድረግ ተጨማሪ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

- *"የመማር ዝግጁነት እንዲኖረኝ አድርጓል፡፡ ጠንካራና ደካማ ጎኔን ለመለየት፡፡ በአእምሮአዊ ክህሎት ላይ ብቻ ሳይሆን እውቀትንና ክህሎትን እንዲሁም አመለካከትን ፣ስሜትን፣ ዝንባሌንና እምነትን ለመመዘንና ለመለየት፡፡ በየትኞቹ ምዕራፎች ጠንካራ እንደሆኑ በየትኞቹ ደግሞ ድክመት እንዳሳየዉ ለመለየትና ድክመት ባሳየሁበት የትኩረት አቅጣጫ እንድንቀይስ፡፡ የተለያዩ ተግባራትን እየወጣን በምናቀርብበት ጊዜ የቋንቋ ችሎታ፣ ፍላጎት፣ የሀሳብ አደረጃጀትና ችሎታ እንዲኖረን፡፡" (ቡድን 4፣ቡድን ቡድን 5፣ቡድን 6)*

6. የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ የተማሪዎችን ተሳትፎ በመከታተል ለሚከናወኑ የተለያዩ የቡድንና የግል ተግባራትን ምጋቤ ምላሽ (አስተያየት) ይሰጣሉ? ለሚለዉ ጥያቄ የተሰጡ ምላሾች፡-

- *"አብዛኛዉ ጊዜ ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ተማሪዎችን ከማነቃቃት አንፃር ተማሪዎች የራሳቸውን ትምህርት የመቆጣጠር ስሜትና እራሳቸውን የመምራት ብቃት እንዲያጎለብቱ ለማስቻል፣ መረጃን ከተማሪዎች ጋር በመነጋገር ሥራ ሲሰሩ በመመልከት የስራቸውን ውጤት ለማግኘት የሚተገብሩት መሆኑንና የሠሯቸውን ሥራዎች እና የሰጡትን መልስ በመመርመር ለተማሪዎች መልሰው የሚያሳውቁበት መንገድ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኛዉ መምህራን ጽሑፋዊ ምላሽ የማይሰጡ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡"* (ገቺ፣ ቦረቻ እና እንግቢ ትምህርት ተማሪዎች)

## 4.2. የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና የአተገባበር ሂደት ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው፡፡ በጥናቱ ሶስት መሪ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

በቅድሚያ ምላሽ ያገኘዉ ጥያቄ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስለ ተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት ያላቸውን ግንዛቤ የሚመለከት ነው፡፡ይህንን ለማረጋገጥ በተደረገው የክፍል ዉስጥ ምልከታ፣ የመምህራን ቃለ-መጠይቅ፣ እንዲሁም የተማሪዎች ቃለ-መጠይቅና የቡድን ተኮር ዉይይት መምህራን ክፍል ዉስጥ በሚገቡበት ወቅት ምን ዓይነት የተከታታይ ምዘና ስልቶችን እንደሚተገብሩ ግልፅ በሆነ አኳሃን በሳምንታዊና ዕለታዊ እቅድ ያዘጋጃሉ፡፡ በጥናቱ መረጃ መሰረት የተገኘ ዉጤት መምህራን ከዓመታዊ ዕቅዳቸዉ ጋር የተጣጣመ ሳምንታዊና ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ በማዉጣት ክፍል ዉስጥ በሚገቡበት ወቅት ምን ዓይነት የተከታታይ ምዘና ስልቶችን እንደሚተገብሩ ቢኖራቸዉም ከሁለት መምህራን በስተቀር በዕቅዱ ላይ የተካተቱትን የተከታታይ ምዘና ሂደቶችም ሆነ ስልቶችን በትክክል አይተገብሩም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ በጥናቱ መልስ ያገኙ ጥያቄዎች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለመመዘን የሚጠቀሙዋቸውን ስልቶች የትኞቹ እንደሆኑና ተከታታይ ምዘናዎችን ሲተገብሩ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች የሚመለከት ነው፡፡ ይህንን ለማረጋገጥ በተደረገው የክፍል ዉስጥ ምልከታ፣ በቃለ-መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት  የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መምህራን የዕለቱን ትምህርት ከመጀመራቸዉ አስቀድመዉ ተማሪዎች በሂደት ስለሚማሩት ትምህርት ዋና ርዕስና ንዑሳን ርዕሶች ያላቸውን ቢያስተዋዉቁም ቀደም ብለዉ ቅድመ ተግባራትንና መልመጃዎችን የማይሰጡ መሆኑን ነው፡፡ መምህራን በሚያስተምሩበት ወቅት በክፍል ውስጥ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን በመስጠት የክፍል ሥራዎችን እየሰጡና ከተማሪዎች ጋር ጥሩ መስተጋብር በመፍጠር በመምህርና በተማሪ መካከል የሚካሄዱ ውይይት ቢያደርጉም የአቻ ግምገማን ግን  ከሁለት መምህራን በስተቀር እየተተገበረ እንዳልሆነ ተረጋግጧል፡፡

የተከታተይ ምዘና ዘዴዎችን ከመጠቀም አንፃር አምስቱ መምህራን የቃል ጥያቄ፣የክፍል ሥራ፣ የቤት ሥራ፣ የግልና የቡድን ሥራ በማሰራት ተማሪዎች የተማሩትን ምን ያህል እንደተገነዘቡትና ያለባቸዉን ችግር ለማወቅ ይጠቀሙበታል፡፡ነገር ግን የተለያዩ ሥራዎች ክምችት የሆነዉን ሰነደ ትምህርት እየተተገበሩ አለመሆኑን ነዉ፡፡ በመጨረሻም መምህራን የተማሪዎችን ተሳትፎ በመከታተል ሰባቱም ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ተማሪዎችን በማነቃቃት ተማሪዎች እራሳቸውን የመምራት ብቃት እንዲያጎለብቱ ቢጠቀሙበትም ጽሑፋዊ ምላሽ የማይሰጡ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ይህም መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለመመዘን የሚጠቀሙዋቸውን ሁለቱንም ስልቶች መሆኑን ነው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና የመፍትሄ ሀሳቦች

በዚህ ምዕራፍ የመጀመሪያው ንኡስ ክፍል የጥናቱን ግኝቶች መሰረት በማድረግ የተሰጡ ማብራሪያዎች ማጠቃለያ የቀረበበት ሲሆን በሚቀጥለው ንኡስ ክፍል ደግሞ የማጠቃለያ ሀሳቦችን መነሻ በማድረግ አስተያየቶችና የመፍትሔ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

## 5.1. ማጠቃለያ

የጥናቱ ዋና አላማ በቡኖ በደሌ ዞን፣2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና የአተገባበር ሂደት ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው፡፡

ጥናቱን ከግብ ለማድረስ ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በቃለ መጠይቅ፣ በክፍል ውስጥ ምልከታና በቡድን ተኮር ውይይት አማካኝነት የተሰበሰበዉ መረጃ በዓይነታዊ የትንተና ዘዴ ተተንትኗል፡፡ በዚሁ መሰረት በተደረገው ትንተናም ጥናቱ ይዟቸው የተነሳቸው አላማዎች ግባቸውን መምታት ችለዋል፡፡ በጥናቱ መረጃ መሰረት የተገኙ ውጤቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

የተተኳሪ ትምህርት ቤቶች መምህራን ሳምንታዊና ዕለታዊ የትምህርት ዕቅድ በማዉጣት ክፍል ዉስጥ በሚገቡበት ወቅት ምን ዓይነት የተከታታይ ምዘና ስልቶችን እንደሚተገብሩ ቢኖራቸዉም ከሁለት መምህራን በስተቀር በዕቅዱ ላይ የተካተቱትን የተከታታይ ምዘና ሂደቶችም ሆነ ስልቶችን በትክክል ስራ ላይ እንደማያዉሉት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

መምህራን የዕለቱን ትምህርት ከመጀመራቸዉ አስቀድመዉ ተማሪዎች በሂደት ስለሚማሩት ትምህርት ዋና ርዕስና ንዑሳን ርዕሶችን ቢያስተዋዉቁም አምስት መምህራን ከተወሰነ ጊዜ ቀደም ብለዉ ለተማሪዎች ተግባራትንና መልመጃዎችን የማይሰጡ መሆኑን ነው፡፡ መምህራን በሚያስተምሩበት ወቅት በብዛት ክፍል ውስጥ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን በመስጠት የክፍል ሥራዎችን እየሰጡና ከተማሪዎች

ጋር ጥሩ መስተጋብር በመፍጠር በመምህርና በተማሪ መካከል የሚካሄዱ ውይይት ቢያደርጉም የአቻ ግምገማን ግን ከሁለት መምህራን በስተቀር እየተተገበረ እንዳልሆነ ጥናቱ ያሳያል፡፡

የተከታተይ ምዘና ዘዴዎችን ከመጠቀም አንፃር መምህራን የቃል ጥያቄ፣የክፍል ሥራ፣ የቤት ሥራ፣ የግልና የቡድን ሥራ በማሰራት ተማሪዎች የተማሩትን ምን ያህል እንደተገነዘቡትና ያለባቸዉን ችግር ለማወቅ ይጠቀሙበታል፡፡ ነገር ግን ሰነደ ትምህርት እየተተገበረ አለመሆኑን ጥናቱ ያሳያል፡፡

በመጨረሻም መምህራን የተማሪዎችን ተሳትፎ በመከታተል ሰባቱም ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት ተማሪዎችን ለማነቃቃት ቢጠቀሙበትም አምስት መምህራን ጽሑፋዊ ምላሽ የማይሰጡ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህም መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለመመዘን የሚጠቀሙዋቸውን ሁለቱንም ስልቶች መሆኑን ነው፡፡ በተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት ካጋጠሟቸው ችግሮች አንፃር ብዙ ተማሪዎች በአንድ ክፍል ውስጥ በመገኘታቸዉ በትክክል ለመተግበር ስለሚያስቸግር ከባድ የስራ ጫናና የክፍለ ጊዜ ብዛት ትግበራዉ ላይ ትልቅ እንቅፋት መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከዚህ የተነሳ ሰባቱም መምህራን ትኩረታቸዉ ውጤት ላይ እንጂ ሂደት ላይ አለመሆኑን ያሳያል፡፡

## 5.2. የመፍትሄ ሀሳቦች

በጥናቱ ውጤቶች ላይ በመመርኮዝ የአማርኛ ትምህርት ተከታታይ ምዘና የአተገባበር ሂደት ለመማር ማስተማር ውጤታማነት ተግባራዊ ለማድረግና እንቅፋት ለሆኑ ጉዳዮች ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሰራባቸዉ የሚከተሉት የመፍትሄ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

- ትምህርት ቤቶቹ ካሉባቸው በርካታ ችግሮች መካከል የመቀመጫ ወንበሮች ምቹ አለመሆንና የተማሪዎች በክፍል ዉስጥ መብዛት ይጠቀሳሉ፡፡ በርካታ ተማሪዎች በጠባብ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ከሆነ መምህራን በክፍል ዉስጥ እንደልብ እየተዘዋወሩ የተከታታይ ምዘናን ለመተግበር ያስቸግራቸዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር ለመቀመጫነት የሚያገለግሉት ወንበሮች በቀላሉ የማይንቀሳቀሱና የተማሪዎችን የግልና የቡድን ስራ ለመከታተል

የማይመቹ ስለሆኑ የተማሪዎች ክፍል ውስጥ መብዛት ችግር ለመቅረፍ የቡኖ በደሌ ዞን ትምህርት ፅህፈት ቤት ከኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት መስተዳድርና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት በቂ የመማሪያ ክፍሎች እንዲሰሩ በማድረግ የማስተማሪያ ክፍሎች ምቹ ቢደረጉና በክፍል ዉስጥ የተማሪዎች ቁጥር ቢቀንስ፡፡

- የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ክህሎት ለማሳደግ የተከታታይ ምዘናን በመጠቀም ማስተማር ጠቀሜታ አለው፡፡ ሆኖም ሰባቱም መምህራን ትኩረታቸዉ ውጤት ላይ እንጂ ሂደት ላይ እንዳልሆነ በሰፊው ይታያል፡፡ ከዚህ ይልቅ ከተማሪዎች አጠቃላይ ሁኔታ ጋር የተመጣጠኑ ምዘናዎችን በመጠቀም ማስተማር ተመራጭ ነው፡፡ ስለሆነም የቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘናን ተጠቅመው አማርኛ ቋንቋን ሲያስተምሩ ትኩረታቸዉ ውጤት ላይ ብቻ ባይሆን ተማሪዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

- ተከታታይ ምዘና አተገባበር ውጤታማ እንዲሆን ተማሪዎች በዕውቀትና በውጤት የተሻለ እንዲሆኑ መምህራን ሁልጊዜ ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው፡፡ በየደረጃው የሚገኙ አካላት የሚያደርጉትን ድጋፍ፣ በተለይ የግንዛቤ እጥረት ላለባቸዉ መምህራን የግንዛቤ መፍጠሪያ ስልጠና መስጠት ቢቻል የተከታታይ ምዘና ስርዓቱ ውጤታማ ሊሆን ይችላል፡፡

- በሁሉም ትምህርት ቤቶች መምህራን እርስ በራሳቸዉ ያላቸዉን ልምድ እንዲለዋወጡ የእርስ በርስ ግምገማ ቢካሄድ የተከታታይ ምዘና አተገባበር ውጤታማ እንዲሆንና በትምህርት ቤት ደረጃ ጠንካራና ደካማ ጎኖች በመለየት መልካም ተሞክሮዎች ለመቀመር ሊጠቅም ይችላል፡፡ ስለዚህ የተከታታይ ምዘናዉን በዕቅድ በመምራት መምህራን ተሞክሮዎችን መቀያየር ቢችሉ የተሻለ ይሆናል፡፡

- በምዘና የተማሪዎችን መማር ለማሻሻል ግብረ መልስ ለተማሪዎች ሲቀርብ ተማሪዎች በትምህርቱ መጀመሪያና መሃል ላይ በጥሩ ሁኔታ እየተማሩ መሆን አለመሆናቸውን ለማወቅና ውጤቱ አጥጋቢ አለመሆኑ ከታወቀ ደግሞ በቶሎ የሚሻሻልበትን ስልት ለመቀየስ ይረዳል፡፡ ስለዚህ መምህራን

የተማሪዎቻቸውን የመረዳት ደረጃ ለመመዘን የሚጠቀሙት በየመንፈቅ ዓመቱ መጨረሻ ላይ የሚያዘጋጁቸውን ፈተናዎች ከሙያ አንጻር ሲታይ ትክክል ባለመሆኑ ሁሉንም የተከታታይ ምዘና ስልቶች በየጊዜዉ ቢተገብሩ የተሻለ ይሆናል፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች

መሀመድ አሊ፡፡ (2002) ፡፡ "በደሴ ከተማ በመንግስትና በግል ትምህርት ቤቶች በሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን መካከል የተከታታይ ምዘና አተገባበር ንጽጽራዊ ጥናት፡፡" የሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

በድሩ ከድር፡፡ (1994)፡፡ የትምህርት ተከታታይ ምዘና ግምገማ ጽንሰ ሃሳቦችና ቴክኒኮች፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ተስፉ አከለ፡፡ (2000) ፡፡ "የአማርኛ ቋንቋ አሰልጣኝ መምህራን የተከታተይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ፣ በትግራይ ክልል በሚገኙ ሦስት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች፡፡" የሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

ተካ ወሌ፡፡ (1998)፡፡ "ተከታታይ ምዘና ለትምህርት ጥራት፡፡" በኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮላጅ ለአጭር ስልጠና የተዘጋጀ /ያልታተመ/፡፡

ታምሩ ፀጋዬ፡፡ (2004)፡፡ "የአማርኛ ቋንቋ አሠልጣኝ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ ሦስት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች"፡፡በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡(ያልታተመ)፡፡

ታጠቁና ሌሎች፡፡ (1995) ፡፡ የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ተከታታይ ምዘና መመሪያ፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

አልማዝ ሃይሌ፡፡(1999)፡፡ "አራተኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት አማርኛን በማስተማር ስነ ዘዴ ትምህርት ለማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)፡፡

*አልማዝ ፍሬው፡፡(2003)፡፡ “በአማራ ክልል የሚገኙ ሁለት የመንግስት የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ፡፡” አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት አማርኛን በማስተማር ስነ ዘዴ ትምህርት ለማስተርስ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)፡፡*

*ኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ፡፡ (2004)፡፡ “ተከታታይ ምዘና እና ተግባራዊ ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ርዕስ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ስልጠና የተዘጋጀ፡፡” አዲስ አበባ፣ (ያልታተመ)፡፡*

*ዳንኤል ዘዉዴ፡፡ (1999)፡፡ “የተከታታይ ምዘና አተገባበር፡፡” ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ፣ ለአጭር ስልጠና የተዘጋጀ (ያልታተመ)፡፡*

*Abiy Yigazaw, (2013). High School teachers' and Students' perception, attitudes actual practices of continuousassessment.htt//www.academic journals.org/ERR*

*AED/BESO II. (2006). “A Concise Manual for Developming and Implementing continuous assessment in Teacher Education Institutions and Primary Schools of Ethiopia.” Addis Ababa,(unpublished).*

*Aggrawal, J. C. (1994). Essential of Educational Psychology. New Delhi: Vikas Publishing Company.*

*Birhanu Moges, (2004). Teacher's assessment of students' performance in selected high school Of Arsi Zone with emphasis on continuous assessment. Unpublished MA Thesis AAU. Faculty of education. Addis Ababa.*

*Brooks, V. (2002). Assessment in Secondary School; Recording, Reporting and Accountability. Buckingham: Open University Press.*

*Capper, J. (1996). Testing to Learn- Learning to Test. Improving Educational Testing In Developing Countries. Washington: International Reading Association Press.*

*Dessalegn Chalchisa. (2004). "Continuouse Assessment in Lower cycle Primary School." IER Flambeau. Vol.12, No.1, PP. 1-8.*

*Elington, H. and Earl, S. (1997). Making Effective use of Continuous Assessment and Portifolios.Shabaan (2001፡19-25)*

Frans, N.,(2007). The role of Continuous assessment in primary school: University of Zululand.

*Hamis, M. (1997). Self Assessment of Language Learning in formal Settings,ELT Journal, vol.51 No, 1. Oxford: Oxford University Press.*

*Ministry of Education. (2003). "Teacher EducationSystem. "Addiss Ababa.*

*Nejabili, A. (1999). Practical guide for Classroom Measurement and testing, the basic essentials. Dares Selaam: Mature Publishers.*

*Nitko, J. A. (2008). Evaluating and Reporting Students Progress, English Language Arts: A Curriculum Guide for Secondary Level-*

*Evaluation Fill://A: English % 20 Language % Arts % 20 A 20 Curriculum % 20 Guide % 20 % for 20 % page 1-7.*

*Puhi C.A. (1997). Develop, Not Judge Continuous Assessment in the ESL Classroom English Teaching Forum vol 35, No.2.*

*Selamneh Zewude, (2011). The practice and challenges of continuous assessment for instructional improvement. Unpublished MA Thesis AAU. Department of curriculum and teachers*

*Teshome Demsie (2001). "Assessment of Pupils Achievements in the Teaching of English Training and practice in focus." The Ethiopian Journal of Education.Vol. 21, No.1, PP.25-47.*

## አባሪዎች

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የማህበራዊ ሳይንስና ስነ-ሰብ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ አማርኛ

## ትምህርት ክፍል

### አባሪ 1፡ለመምህራን የቀረቡ የቃለ-መጠይቅ ጥያቄዎች

የተከበሩ መምህር/ርት፦

የዚህ ቃለ-መጠይቅ ዋና ዓላማ በቡኖ በደሌ ዞን፣ 2ተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት ምን እንደሚመስል መረጃ ለመሰብሰብ ነዉ፡፡ በመሆኑም ተገቢውን መረጃ በመስጠት እንዲተባበሩኝ በትህትና እጠይቃለዉ፡፡

የት/ቤት ስም፦______________ ቃለ-መጠይቁ የተካሄደበት ቦታ፦______________

ስም፦______________ ጾታ፦___ ዕድሜ፦____

የትምህርት ደረጃ፦______________ የአገልግሎት ዘመን፦______________

1. ተከታታይ ምዘና ለእርሶ ምን ማለት ነዉ? እንዴት እንደተረዱት ቢገልፁልኝ?

2. ከተከታታይ ምዘና ጋር በተያያዘ ስልጠና ተሳትፈው ያውቃሉ? መልስዎ አዎ ከሆነ የሥልጠናዉ ይዘቶች ምን ምን ነበሩ? ስልጠናዉ በቂ ነበር ብለዉ ያስባሉ?

3. የተከታታይ ምዘናው ሥልጠና በተከታታይ ምዘና አተገባበርዎ ላይ ያመጣው ለውጥ ካለ ሀሳብዎን ቢገልፁልኝ?

4. የተከታታይ ምዘናን እንዴት ይተገብራሉ? የሚተገብሩት የምዘና ዓይነት የትኛዉ ነዉ?

5. በተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች (ደካማ-ጎኖች) ካሉ? የተገኙ ዉጤቶች (ጠንካራ-ጎኖች) ካሉ?

6. በት/ቤታችሁ የተከታታይ ምዘና አተገባበር የተቀመጠውን ግብና ዓላማ ከማሳካትና የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ከማርካት አንጻር ምን ይመስላል?

## አባሪ 2፡ ለተማሪዎች የቀረቡ የቃለ-መጠይቅ ጥያቄዎች

የዚህ ቃለ-መጠይቅ ዋና ዓላማ በቡኖ በደሌ ዞን 2ተኛ ደረጃ ት/ቤቶች 9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት ምን እንደሚመስል መረጃ ለመሰብሰብ ነዉ፡፡ በመሆኑም ተገቢውን መረጃ በመስጠት እንድትተባበረኝ/ሪኝ በትህትና እጠይቃለዉ፡፡

የት/ቤት ስም፡-______________ ቃለ-መጠይቁ የተካሄደበት ቦታ፡-______________

ስም፡-______________ ጾታ፡-___ ዕድሜ፡-_____ ክፍልና ሴክሽን፡-_______

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ የዕለቱን ትምህርት ከማስተማራቸዉ በፊት ስለሚያስተምሩት ትምህርት ዋና ርዕስና ንዑሳን ርዕሶችን ያስተዋዉቃሉ?

2. የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ በክፍል ዉስጥ ምን ዓይነት የምዘና ስልቶችን ይጠቀማሉ?

3. የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ በሚያስተምሩበት ጊዜ ክፍል ዉስጥ እየተዘዋወሩ ክትትል ያደርጋሉ? መልስህ/ሽ አዎ ከሆነ በክትትሉ ወቅት ምን ምን ይተገብራሉ?

4. የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ የተለያዩ የግልና የቡድን ተግባራትን ይሰጣሉ? ያርማሉ? ምን ያህል ውጤት መያዝ እንዳለባቸው ተወያይታችዉ ትወስናላችዉ?

5. የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ በተለያዩ ጊዜያት የሚሰጧቸዉ የቤት ስራዎችና የቡድን ስራዎች የአማርኛ ቋንቋ ችሎታህ/ሽን የተሻለ አድርገዋል ብለህ/ሽ ታስባለህ/ሽ? እንዴት?

6. የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ የተማሪዎችን ተሳትፎ በመከታተል ለሚከናወኑ የተለያዩ የቡድንና የግል ተግባራትን ምጋቤ ምላሽ (አስተያየት) ይሰጣሉ?

## አባሪ 3፡ ለተማሪዎች የቀረቡ የቡድን ተኮር ውይይት ጥያቄዎች

ዉድ ተማሪዎች፦

የዚህ የቡድን ውይይት ዋና ዓላማ በቡኖ በደሌ ዞን፣ 2ተኛ ደረጃ ት/ቤቶች 9ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ሂደት ምን እንደሚመስል መረጃ ለመሰብሰብ ነዉ፡፡ በመሆኑም ከጓደኞቻችሁ ጋር በመሆን ሀሳብ በመስጠት እንድትተባበሩ በትህትና እጠይቃለዉ፡፡

1.የአማርኛ ቋንቋ መምህራችዉ ከማስተማር በፊት፣በሚያስተምሩበት ጊዜና ከማስተማር በኋላ ክፍል ምን ዓይነት ሂደት ይጠቀማሉ?

2.የአማርኛ ቋንቋ መምህራችዉ በክፍል ዉስጥ ምን ዓይነት የተከታታይ ምዘና ስልቶችን ይጠቀማሉ?

3.የአማርኛ ቋንቋ መምህራችዉ በተከታታይ ምዘና ሂደት የሰጡትን የግልና የቡድን ስራዎች ያርማሉ? ለምታከናዉኗቸዉ ተግባራት ምጋቤ ምላሽ (አስተያየት) ይሰጣሉ?

4. የአማርኛ ቋንቋ መምህራችዉ በክፍል ዉስጥ የሚተገብሩት የምዘና ስልቶች በአማርኛ ቋንቋ ዕዉቀታችዉ ላይ ያመጣዉን ለዉጥ እንዴት ታዩታለችዉ?

## አባሪ 4፡ የክፍል ውስጥ ምልከታ መከታተያ ቅፅ

ከዚህ በታች ለመከታተያነት የቀረቡ ጥያቄዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚከናወኑትን የተከታተይ ምዘና ሂደት ለመፈተሽ የተዘጋጁ ሲሆን ለሁሉም ምልከታዎች ያገለግላሉ፡፡

የት/ቤት ስም፦_____________ ምልከታ የተደረገበት፦________

ቀን፦_____________ መምህር/ርት፦_____________

ክፍል-ጊዜ፦_______ ሰዓት፦________ ፈረቃ፦_______

የትምህርት ርዕስ፦_____________ የተማሪዎች ብዛት፦ወ፡__ሴ፡__ ድ፡___

| ተ/ቁ | የመምህሩ ተግባር | አማራጮች | |
|---|---|---|---|
| | | ተከናውኗል | አልተከናወነም |
| 1) | ከማስተማር ሂደት በፊት የመምህሩ ተግባር | | |
| 1.1. | ዋና ርዕስና ንዑሳን ርዕሶችን ማሳወቅ | | |
| 1.2. | ቅድመ ፈተና መስጠት | | |
| 2) | በመማር ማስተማር ሂደት የመምህሩ ተግባር | | |
| 2.1. | የክፍል ሥራ ማሰራት | | |
| 2.2. | እየተዘዋወረ ክትትል ማድረግ | | |
| 2.3. | የጓደኛ ለጓደኛ ምዘና እንዲካሄድ ማድረግ | | |
| 2.4. | ተማሪዎች እየወጡ እንዲያቀርቡ ማድረግ | | |
| 2.5. | ከተማሪዎች ጋር ጥሩ መስተጋብር መፍጠር (የመምህር ተማሪ ውይይት ማካሄድ) | | |
| 2.6. | ተማሪዎች ራሳቸውን እንዲገመግሙ ማድረግ | | |
| 3) | የተከታተይ ምዘና ዘዴዎችን መጠቀም | | |
| 3.1. | የቃል ጥያቄ ማካሄድ | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3.2. | የቤት ሥራ መስጠት | | |
| 3.3. | የቡድን ተግባራትን ማሰራት | | |
| 3.4. | የግል ሥራን ማሰራት | | |
| 3.5. | ሙከራና ፈተና መስጠት | | |
| 4) | የተማሪዎችን ተሳትፎ በመከታተል ምጋቤ ምላሽ (አስተያየት) መስጠት | | |
| 4.1. | ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ መስጠት | | |
| 4.2. | ጽሑፋዊ ምላሽ መስጠት | | |

## አባሪ 5፡የክፍል ውስጥ ምልከታ

**የክፍል ምልከታ-1**

የት/ቤት ስም፦ቦረቻ 2ተኛ ደረጃ ት/ቤት ምልከታ የተደረገበት፦9ኛA

ቀን፦2/08/2011 ዓ.ም መምህር/ርት፦መሰረት ገዛሀኝ

ክፍለ-ጊዜ፦2ኛ ሰዓት፦2፡40-3፡20

ፈረቃ፦ጠዋት

የትምህርት ርዕስ፦ስነ ግጥም የተማሪዎች ብዛት፦ወ፡34 ሴ፡25

ድ፡59

ዕለቱ ረቡዕ ነዉ፡፡ መምህሯ ለተማሪዎች ሰላምታ አቅርበዉ የዕለቱን ዋና ርዕስ "የአረፍተ ነገር ክፍሎች" ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ንዑሳን ርዕሶችን በማስተዋወቅ አላማዉን በአጭሩ አብራሩ፡፡ በማስከተልም ተማሪዎች በቡድን በመሆን እንዲወያዩበት በማዘዝ የተወያዩበትን ሀሳብ ለክፍሉ እንዲያቀርቡ በማድረግ በመማሪያ መጽሀፋቸው ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎችን በጥያቄና መልስ መልክ እንዲወያዩ አድርገዋል፡፡ ከዚያም የግልና የክፍል ሥራዎችን በመስጠት ሲጨርሱም ለመምህሩ እንዲያሳዩ ተደርጓል፡፡ በሚያስተምሩበት ወቅት ከተማሪዎች ጋር ጥሩ መስተጋብር በመፍጠር የቃል ጥያቄ ይጠይቁ ነበር፡፡ በዕለቱ ከ 5% የሚታረም ነዉ በማለት ለሙከራ የሚሆን በርዕሱ ዙሪያ ፈተና(ቴስት) ሰጧቸዉ፡፡ በመጨረሻም ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ከሰጡ በኋላ የቤት ስራ ሰጥተዉ ክፍሉን ለቀዉ ወጡ፡፡

**የክፍል ምልከታ-2**

የት/ቤት ስም፦ቦረቻ 2ተኛ ደረጃ ት/ቤት ምልከታ የተደረገበት፦9ኛC

ቀን፦4/08/2011 ዓ.ም መምህር/ርት፦መሰረት ገዛሀኝ

ክፍለ-ጊዜ፦5ኛ ሰዓት፦5፡05-5፡45

ፈረቃ፦ጠዋት

የትምህርት ርዕስ፦ስነ ግጥም የተማሪዎች ብዛት፦ወ፡29 ሴ፡31

ድ፡60

ዕለቱ አርብ ነዉ፡፡ መምህሯ ለተማሪዎች ሰላምታ አቅርበዉ የዕለቱን ዋና ርዕስ "የአረፍተ ነገር ክፍሎች" ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ንዑሳን ርዕሶችን በማስተዋወቅ አላማዉን በአጭሩ አብራሩ፡፡ በማስከተልም ተማሪዎች በቡድን በመሆን እንዲወያዩበት በማዘዝ የተወያዩበትን ሀሳብ ለክፍሉ እንዲያቀርቡ በማድረግ በመማሪያ መጽሀፋቸው ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎችን በጥያቄና መልስ መልክ እንዲወያዩ አድርገዋል፡፡ ከዚያም የግልና የክፍል ሥራዎችን በመስጠት ሲጨርሱም ለመምህሩ እንዲያሳዩ ተደርጓል፡፡በሚያስተምሩበት ወቅት ከተማሪዎች ጋር ጥሩ መስተጋብር በመፍጠር የቃል ጥያቄ ይጠይቁ ነበር፡፡ በመጨረሻም ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ከሰጡ በኋላ የቤት ስራ ሰጥተዉ ክፍሉን ለቀዉ ወጡ፡፡

**የክፍል ምልከታ-3**

የት/ቤት ስም፦ቦረቻ 2ተኛ ደረጃ ት/ቤት ምልከታ የተደረገበት፦9ኛH

ቀን፦2/08/2011 ዓ.ም መምህር/ርት፦ወርቁ ጥጋቡ

ክፍለ-ጊዜ፦4ኛ ሰዓት፦4፡25-5፡05

ፈረቃ፦ጠዋት

የትምህርት ርዕስ፦የተዉኔት ምንነት የተማሪዎች ብዛት፦ወ፡25 ሴ፡27 ድ፡52

ዕለቱ ረቡዕ ነዉ፡፡ መምህሯ ለተማሪዎች ሰላምታ አቅርበዉ የዕለቱን ዋና ርዕስ "የአረፍተ ነገር ክፍሎች" ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ንዑሳን ርዕሶችን በማስተዋወቅ አላማዉን በአጭሩ አብራሩ፡፡ በማስከተልም ተማሪዎች በቡድን በመሆን እንዲወያዩበት በማዘዝ የተወያዩበትን ሀሳብ ለክፍሉ እንዲያቀርቡ በማድረግ በመማሪያ መጽሀፋቸው ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎችን በጥያቄና መልስ መልክ እንዲወያዩ አድርገዋል፡፡ ከዚያም የግልና የክፍል ሥራዎችን በመስጠት ሲጨርሱም ለመምህሩ እንዲያሳዩ ተደርጓል፡፡በሚያስተምሩበት ወቅት ከተማሪዎች ጋር ጥሩ መስተጋብር በመፍጠር የቃል ጥያቄ ይጠይቁ ነበር፡፡ በመጨረሻም ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ከሰጡ በኋላ የዕለቱን ትምህርት በማጠቃለል የቤት ስራ በመስጠት ክፍሉን ለቀዉ ወጡ፡፡

**የክፍል ምልከታ-4**

የት/ቤት ስም፦ቦረቻ 2ተኛ ደረጃ ት/ቤት ምልከታ የተደረገበት፦9ኛI

ቀን፦4/08/2011 ዓ.ም መምህር/ርት፦ወርቄ ጥጋቡ

ክፍለ-ጊዜ፦1ኛ ሰዓት፦2፡00-2፡40

ፈረቃ፦ጠዋት

የትምህርት ርዕስ፦የተዉኔት ምንነት የተማሪዎች ብዛት፦ወ፡32 ሴ፡30

ድ፡62

ዕለቱ አርብ ነዉ፡፡ መምህሯ ለተማሪዎች ሰላምታ አቅርበዉ የዕለቱን ዋና ርዕስ "የአረፍተ ነገር ክፍሎች" ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ንዑሳን ርዕሶችን በማስተዋወቅ አላማዉን በአጭሩ አብራሩ፡፡ በማስከተልም ተማሪዎች በቡድን በመሆን እንዲወያዩበት በማዘዝ የተወያዩበትን ሀሳብ ለክፍሉ እንዲያቀርቡ በማድረግ በመማሪያ መጽሀፋቸው ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎችን በጥያቄና መልስ መልክ እንዲወያዩ አድርገዋል፡፡ ከዚያም የግልና የክፍል ሥራዎችን በመስጠት ሲጨርሱም ለመምህሩ እንዲያሳዩ ተደርጓል፡፡በሚያስተምሩበት ወቅት ከተማሪዎች ጋር ጥሩ መስተጋብር በመፍጠር የቃል ጥያቄ ይጠይቁ ነበር፡፡ በመጨረሻም ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ከሰጡ በኋላ የቤት ስራ ሰጥተዉ ክፍሉን ለቀዉ ወጡ፡፡

**የክፍል ምልከታ-5**

የት/ቤት ስም፦ገቺ 2ተኛ ደረጃ ት/ቤት ምልከታ የተደረገበት፦9ኛG

ቀን፦1/08/2011 ዓ.ም መምህር/ርት፦መሰረት ማህባዉ

ክፍለ-ጊዜ፦2ኛ ሰዓት፦2፡40-3፡20 ፈረቃ፦ጠዋት

የትምህርት ርዕስ፦አከባቢያችን የተማሪዎች ብዛት፦ወ፡24 ሴ፡31

ድ፡55

ዕለቱ ማክሰኞ ነዉ፡፡ መምህሯ ለተማሪዎች ሰላምታ አቅርበዉ የዕለቱን ዋና ርዕስ "የአረፍተ ነገር ክፍሎች" ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ንዑሳን ርዕሶችን በማስተዋወቅ አላማዉን በአጭሩ አብራሩ፡፡ በማስከተልም ተማሪዎች በቡድን በመሆን እንዲወያዩበት በማዘዝ የተወያዩበትን ሀሳብ ለክፍሉ እንዲያቀርቡ በማድረግ በመማሪያ መጽሀፋቸው ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎችን በጥያቄና መልስ መልክ እንዲወያዩ አድርገዋል፡፡ ከዚያም የግልና የክፍል ሥራዎችን በመስጠት ሲጨርሱም ለመምህሩ እንዲያሳዩ ተደርጓል፡፡ በሚያስተምሩበት ወቅት ከተማሪዎች ጋር ጥሩ መስተጋብር በመፍጠር የቃል ጥያቄ ይጠይቁ ነበር፡፡ በመጨረሻም ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ከሰጡ በኋላ የቤት ስራ ሰጥተዉ ክፍሉን ለቀዉ ወጡ፡፡

**የክፍል ምልከታ-6**

የት/ቤት ስም፦ገቺ 2ተኛ ደረጃ ት/ቤት ምልከታ የተደረገበት፦9ኛH

ቀን፦3/08/2011 ዓ.ም መምህር/ርት፦መሰረት ማሀባዉ

ክፍለ-ጊዜ፦6ኛ ሰዓት፦5፡45-6፡25 ፈረቃ፦ጠዋት

የትምህርት ርዕስ፦አከባቢያችን የተማሪዎች ብዛት፦ወ፡30 ሴ፡21 ድ፡51

ዕለቱ ሐሙስ ነዉ፡፡ መምህሯ ለተማሪዎች ሰላምታ አቅርበዉ የዕለቱን ዋና ርዕስ "የአረፍተ ነገር ክፍሎች" ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ንዑሳን ርዕሶችን በማስተዋወቅ አላማዉን በአጭሩ አብራሩ፡፡ በማስከተልም ተማሪዎች በቡድን በመሆን እንዲወያዩበት በማዘዝ የተወያዩበትን ሀሳብ ለክፍሉ እንዲያቀርቡ በማድረግ በመማሪያ መጽሀፋቸው ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎችን በጥያቄና መልስ መልክ እንዲወያዩ አድርገዋል፡፡ ከዚያም የግልና የክፍል ሥራዎችን በመስጠት ሲጨርሱም ለመምህሩ እንዲያሳዩ ተደርጓል፡፡በሚያስተምሩበት ወቅት ከተማሪዎች ጋር ጥሩ መስተጋብር በመፍጠር የቃል ጥያቄ ይጠይቁ ነበር፡፡ በመጨረሻም ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ከሰጡ በኋላ የቤት ስራ ሰጥተዉ ክፍሉን ለቀዉ ወጡ፡፡

### የክፍል ምልከታ-7

የት/ቤት ስም፦ገቺ 2ተኛ ደረጃ ት/ቤት ምልከታ የተደረገበት፦9ኛB

ቀን፦1/08/2011 ዓ.ም መምህር/ርት፦እህትነሽ ታረቀኝ

ክፍለ-ጊዜ፦3ኛ ሰዓት፦3፡20-4፡00 ፈረቃ፦ጠዋት

ዕለቱ ማክሰኞ ነዉ፡፡ መምህሯ ለተማሪዎች ሰላምታ አቅርበዉ የዕለቱን ዋና ርዕስ "የአረፍተ ነገር ክፍሎች" ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ንዑሳን ርዕሶችን በማስተዋወቅ አላማዉን በአጭሩ አብራሩ፡፡ በማስከተልም ተማሪዎች በቡድን በመሆን እንዲወያዩበት በማዘዝ የተወያዩበትን ሀሳብ ለክፍሉ እንዲያቀርቡ በማድረግ በመማሪያ መጽሀፋቸው ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎችን በጥያቄና መልስ መልክ እንዲወያዩ አድርገዋል፡፡ ከዚያም የግልና የክፍል ሥራዎችን በመስጠት ሲጨርሱም ለመምህሩ እንዲያሳዩ ተደርጓል፡፡ በሚያስተምሩበት ወቅት ከተማሪዎች ጋር ጥሩ መስተጋብር በመፍጠር የቃል ጥያቄ ይጠይቁ ነበር፡፡ በመጨረሻም ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ከሰጡ በኋላ የቤት ስራ ሰጥተዉ ክፍሉን ለቀዉ ወጡ፡፡

### የክፍል ምልከታ-8

የት/ቤት ስም፦ገቺ 2ተኛ ደረጃ ት/ቤት ምልከታ የተደረገበት፦9ኛD

ቀን፦3/08/2011 ዓ.ም መምህር/ርት፦እህትነሽ ታረቀኝ

ክፍለ-ጊዜ፦1ኛ ሰዓት፦2፡00-2፡40 ፈረቃ፦ጠዋት

ዕለቱ ሐሙስ ነዉ፡፡ መምህሯ ለተማሪዎች ሰላምታ አቅርበዉ የዕለቱን ዋና ርዕስ "የአረፍተ ነገር ክፍሎች" ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ንዑሳን ርዕሶችን በማስተዋወቅ አላማዉን በአጭሩ አብራሩ፡፡ በማስከተልም ተማሪዎች በቡድን በመሆን እንዲወያዩበት በማዘዝ የተወያዩበትን ሀሳብ ለክፍሉ እንዲያቀርቡ በማድረግ በመማሪያ መጽሀፋቸው ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎችን በጥያቄና መልስ መልክ እንዲወያዩ አድርገዋል፡፡ ከዚያም የግልና የክፍል ሥራዎችን በመስጠት ሲጨርሱም ለመምህሩ እንዲያሳዩ ተደርጓል፡፡በሚያስተምሩበት ወቅት ከተማሪዎች ጋር ጥሩ መስተጋብር በመፍጠር የቃል ጥያቄ ይጠይቁ ነበር፡፡

በመጨረሻም ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ከሰጡ በኋላ የቤት ስራ ሰጥተዉ ክፍሉን ለቀዉ ወጡ፡፡

**የክፍል ምልከታ-9**

የት/ቤት ስም፦እንግቢ 2ተኛ ደረጃ ት/ቤት ምልከታ የተደረገበት፦9ኛA

ቀን፦2/08/2011 ዓ.ም መምህር/ርት፦ አዲሱ መሰለ

ክፍለ-ጊዜ፦5ኛ ሰዓት፦5፡05-5፡45

ፈረቃ፦ጠዋት

ዕለቱ ረቡዕ ነዉ፡፡ መምህሩ ለተማሪዎች ሰላምታ አቅርበዉ የዕለቱን ዋና ርዕስ "የአረፍተ ነገር ክፍሎች" ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ንዑሳን ርዕሶችን በማስተዋወቅ አላማዉን በአጭሩ አብራሩ፡፡ በማስከተልም ተማሪዎች በቡድን በመሆን እንዲወያዩበት በማዘዝ የተወያዩበትን ሀሳብ ለክፍሉ እንዲያቀርቡ በማድረግ በመማሪያ መጽሀፋቸው ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎችን በጥያቄና መልስ መልክ እንዲወያዩ አድርገዋል፡፡ ከዚያም የግልና የክፍል ሥራዎችን በመስጠት ሲጨርሱም ለመምህሩ እንዲያሳዩ ተደርጓል፡፡በሚያስተምሩበት ወቅት ከተማሪዎች ጋር ጥሩ መስተጋብር በመፍጠር የቃል ጥያቄ ይጠይቁ ነበር፡፡ በመጨረሻም ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ከሰጡ በኋላ የቤት ስራ ሰጥተዉ ክፍሉን ለቀዉ ወጡ፡፡

**የክፍል ምልከታ-10**

የት/ቤት ስም፦እንግቢ 2ተኛ ደረጃ ት/ቤት ምልከታ የተደረገበት፦9ኛD

ቀን፦2/08/2011 ዓ.ም መምህር/ርት፦አዲሱ መሰለ

ክፍለ-ጊዜ፦3ኛ ሰዓት፦3፡20-4፡00 ፈረቃ፦ጠዋት

ዕለቱ ረቡዕ ነዉ፡፡ መምህሩ ለተማሪዎች ሰላምታ አቅርበዉ የዕለቱን ዋና ርዕስ "የአረፍተ ነገር ክፍሎች" ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ንዑሳን ርዕሶችን በማስተዋወቅ

አላማዉን በአጭሩ አብራሩ፡፡ በማስከተልም ተማሪዎች በቡድን በመሆን እንዲወያዩበት በማዘዝ የተወያዩበትን ሀሳብ ለክፍሉ እንዲያቀርቡ በማድረግ በመማሪያ መጽሀፋቸው ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎችን በጥያቄና መልስ መልክ እንዲወያዩ አድርገዋል፡፡ ከዚያም የግልና የክፍል ሥራዎችን በመስጠት ሲጨርሱም ለመምህሩ እንዲያሳዩ ተደርጓል፡፡ በሚያስተምሩበት ወቅት ከተማሪዎች ጋር ጥሩ መስተጋብር በመፍጠር የቃል ጥያቄ ይጠይቁ ነበር፡፡ በመጨረሻም ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ከሰጡ በኋላ ክፍሉን ለቀዉ ወጡ፡፡

**የክፍል ምልከታ-11**

| | |
|---|---|
| የት/ቤት ስም፡-እንግቢ 2ተኛ ደረጃ ት/ቤት | ምልከታ የተደረገበት፡-9ኛF |
| ቀን፡-2/08/2011 ዓ.ም | መምህር/ርት፡-ጌታነህ ታደሰ |
| ክፍለ-ጊዜ፡-1ኛ | ሰዓት፡-6፡45-7፡25 ፈረቃ፡-ከሰዓት |

ዕለቱ ረቡዕ ነዉ፡፡ መምህሩ ለተማሪዎች ሰላምታ አቅርበዉ የዕለቱን ዋና ርዕስ "የአረፍተ ነገር ክፍሎች" ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ንዑሳን ርዕሶችን በማስተዋወቅ አላማዉን በአጭሩ አብራሩ፡፡ በማስከተልም ተማሪዎች በቡድን በመሆን እንዲወያዩበት በማዘዝ የተወያዩበትን ሀሳብ ለክፍሉ እንዲያቀርቡ በማድረግ በመማሪያ መጽሀፋቸው ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎችን በጥያቄና መልስ መልክ እንዲወያዩ አድርገዋል፡፡ ከዚያም የግልና የክፍል ሥራዎችን በመስጠት ሲጨርሱም ለመምህሩ እንዲያሳዩ ተደርጓል፡፡በሚያስተምሩበት ወቅት ከተማሪዎች ጋር ጥሩ መስተጋብር በመፍጠር የቃል ጥያቄ ይጠይቁ ነበር፡፡ በመጨረሻም ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ከሰጡ በኋላ ክፍሉን ለቀዉ ወጡ፡፡

**የክፍል ምልከታ-12**

የት/ቤት ስም፡-እንግቢ 2ተኛ ደረጃ ት/ቤት ምልከታ የተደረገበት፡-9ኛG

ቀን፡-2/08/2011 ዓ.ም መምህር/ርት፡-ጌታነህ ታደሰ

ክፍለ-ጊዜ፡-4ኛ ሰዓት፡-9፡00-9፡40

ፈረቃ፡-ከሰዓት

ዕለቱ ረቡዕ ነዉ፡፡ መምህሩ ለተማሪዎች ሰላምታ አቅርበዉ የዕለቱን ዋና ርዕስ "የአረፍተ ነገር ክፍሎች" ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ንዑሳን ርዕሶችን በማስተዋወቅ አላማዉን በአጭሩ አብራሩ፡፡ በማስከተልም ተማሪዎች በቡድን በመሆን እንዲወያዩበት በማዘዝ የተወያዩበትን ሀሳብ ለክፍሉ እንዲያቀርቡ በማድረግ በመማሪያ መጽሀፋቸው ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎችን በጥያቄና መልስ መልክ እንዲወያዩ አድርገዋል፡፡ ከዚያም የግልና የክፍል ሥራዎችን በመስጠት ሲጨርሱም ለመምህሩ እንዲያሳዩ ተደርጓል፡፡በሚያስተምሩበት ወቅት ከተማሪዎች ጋር ጥሩ መስተጋብር በመፍጠር የቃል ጥያቄ ይጠይቁ ነበር፡፡ በመጨረሻም ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ከሰጡ በኋላ ክፍሉን ለቀዉ ወጡ፡፡

**የክፍል ምልከታ-13**

የት/ቤት ስም፡-እንግቢ 2ተኛ ደረጃ ት/ቤት ምልከታ የተደረገበት፡-9ኛH

ቀን፡-9/08/2011 ዓ.ም መምህር/ርት፡-ልጅአገኘዉ ብሩ

ክፍለ-ጊዜ፡-3ኛ ሰዓት፡-3፡20-4፡00

ፈረቃ፡-ጠዋት

ዕለቱ ረቡዕ ነዉ፡፡ መምህሩ ለተማሪዎች ሰላምታ አቅርበዉ የዕለቱን ዋና ርዕስ "የአረፍተ ነገር ክፍሎች" ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ንዑሳን ርዕሶችን በማስተዋወቅ አላማዉን በአጭሩ አብራሩ፡፡ በማስከተልም ተማሪዎች በቡድን በመሆን እንዲወያዩበት በማዘዝ የተወያዩበትን ሀሳብ ለክፍሉ እንዲያቀርቡ በማድረግ በመማሪያ መጽሀፋቸው ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎችን በጥያቄና መልስ መልክ እንዲወያዩ አድርገዋል፡፡ ከዚያም የግልና የክፍል ሥራዎችን በመስጠት ሲጨርሱም ለመምህሩ እንዲያሳዩ ተደርጓል፡፡ በሚያስተምሩበት ወቅት

ከተማሪዎች ጋር ጥሩ መስተጋብር በመፍጠር የቃል ጥያቄ ይጠይቁ ነበር፡፡ በመጨረሻም ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ከሰጡ በኋላ ክፍሉን ለቀዉ ወጡ፡፡

**የክፍል ምልከታ-14**

የት/ቤት ስም፦እንግቢ 2ተኛ ደረጃ ት/ቤት ምልከታ የተደረገበት፦9ኛ|

ቀን፦9/08/2011 ዓ.ም መምህር/ርት፦ልጅአገኘዉ ብሩ

ክፍለ-ጊዜ፦4ኛ ሰዓት፦4፡25-5፡05

ፈረቃ፦ጠዋት

ዕለቱ ረቡዕ ነዉ፡፡ መምህሩ ለተማሪዎች ሰላምታ አቅርበዉ የዕለቱን ዋና ርዕስ "የአረፍተ ነገር ክፍሎች" ጥቁር ሰሌዳ ላይ በመፃፍ ንዑሳን ርዕሶችን በማስተዋወቅ አላማዉን በአጭሩ አብራሩ፡፡ በማስከተልም ተማሪዎች በቡድን በመሆን እንዲወያዩበት በማዘዝ የተወያዩበትን ሀሳብ ለክፍሉ እንዲያቀርቡ በማድረግ በመማሪያ መጽሀፋቸው ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎችን በጥያቄና መልስ መልክ እንዲወያዩ አድርገዋል፡፡ ከዚያም የግልና የክፍል ሥራዎችን በመስጠት ሲጨርሱም ለመምህሩ እንዲያሳዩ ተደርጓል፡፡ በሚያስተምሩበት ወቅት ከተማሪዎች ጋር ጥሩ መስተጋብር በመፍጠር የቃል ጥያቄ ይጠይቁ ነበር፡፡ በመጨረሻም ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ከሰጡ በኋላ ክፍሉን ለቀዉ ወጡ፡፡

## አባሪ 6

## በቃለ-መጠይቅ የተሳተፉ መምህራን ዝርዝር

| ተ/ቁ | ስም | ጾታ | ዕድሜ | የት/ቤት ስም | የት/ት ደረጃ | የስራ ልምድ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | መሰረት ገዛሀኝ | ሴ | 32 | ቦረቻ | የመጀመሪያ ድግሪ | 14 ዓመት |
| 2 | ወርቄ ጥጋቡ | ሴ | 24 | ቦረቻ | የመጀመሪያ ድግሪ | 3 ዓመት |
| 3 | እህትነሽ ታረቀኝ | ሴ | 31 | ገቺ | የመጀመሪያ ድግሪ | 14 ዓመት |
| 4 | መሰረት ማህባዉ | ሴ | 30 | ገቺ | የመጀመሪያ ድግሪ | 13 ዓመት |
| 5 | አዲሱ መሰለ | ወ | 33 | እንግቢ | የመጀመሪያ ድግሪ | 15 ዓመት |
| 6 | ጌታነህ ታደሰ | ወ | 32 | እንግቢ | የመጀመሪያ ድግሪ | 14 ዓመት |
| 7 | ልጅአገኘዉ ብሩ | ወ | 49 | እንግቢ | የመጀመሪያ ድግሪ | 32 ዓመት |

## አባሪ 7

## በቃል-መጠይቅ የተሳተፉ ተማሪዎች ዝርዝር

| ተ/ቁ | ስም | ጾታ | ዕድሜ | የት/ቤት ስም | ክፍልና ሴክሽን |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሙስሊማ ዜኑ | ሴ | 15 | ቦረቻ | 9ኛA |
| 2 | ሀብታሙ ግዛዉ | ወ | 16 | ቦረቻ | 9ኛC |
| 3 | ትዕግስት አዲሱ | ሴ | 16 | ቦረቻ | 9ኛI |
| 4 | ገብሬ ቀነአ | ወ | 17 | ገቺ | 9ኛB |
| 5 | ህይወት ሺፈራዉ | ሴ | 15 | ገቺ | 9ኛC |
| 6 | ዳሩሰላም ተካልኝ | ወ | 16 | ገቺ | 9ኛG |
| 7 | ብሩክታየት ጥላሁን | ሴ | 15 | እንግቢ | 9ኛD |
| 8 | ካሳሁን ብሩ | ወ | 16 | እንግቢ | 9ኛE |
| 9 | ዝናቡ ታየ | ወ | 16 | እንግቢ | 9ኛF |

## አባሪ 8

## በቡድን ተኮር ውይይት የተሳተፉ የቦረቻ ት/ቤት ተማሪዎች

| ተ/ቁ | ስም | ጾታ | መለያ | ብዛት | ውይይቱ የተካሄደበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሱራፌል ምህረቱ | ወ | ቡድን-1 | 7 | 10/08/2011 ዓ.ም |
| 2 | አበባዉ ምስጋናዉ | ሴ | | | |
| 3 | አያት እብራሂም | ሴ | | | |
| 4 | አቡያዚድ ያያ | ወ | | | |
| 5 | ግዲ ሸሪፍ | ወ | | | |
| 6 | ሙስሊማ ሸሪፍ | ሴ | | | |
| 7 | አብደላ ፍቃዱ | ወ | | | |
| 8 | ሰዒዶ ከማል | ሴ | ቡድን-2 | 8 | 10/08/2011 ዓ.ም |
| 9 | መሃመድ መሀድ | ወ | | | |
| 10 | ዘቢባ እሸቱ | ሴ | | | |
| 11 | ሀብታሙ ሙላቱ | ወ | | | |
| 12 | ሀገሬ አማረ | ሴ | | | |
| 13 | ጥሩ አይናለም | ሴ | | | |
| 14 | ጀብር መኑ | ወ | | | |
| 15 | ቶፊቅ ከማል | ወ | | | |

# አባሪ 9

## በቡድን ተኮር ውይይት የተሳተፉ የገቺ ት/ቤት ተማሪዎች

| ተ/ቁ | ስም | ጾታ | መለያ | ብዛት | ውይይቱ የተካሄደበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አብዱላፊዝ ታየ | ወ | ቡድን-3 | 7 | 11/08/2011 ዓ.ም |
| 2 | ትንሳዔ ታሪኩ | ሴ | | | |
| 3 | ፋሚ ጀማል | ወ | | | |
| 4 | ሬድዋን ኑሩ | ወ | | | |
| 5 | ቅድስት ባየ | ሴ | | | |
| 6 | ሴፉዲን ታጁ | ወ | | | |
| 7 | ሳምራዊት ተስፋየ | ሴ | | | |
| 8 | ትንሳኤነሽ አወቀ | ሴ | ቡድን-4 | 7 | 11/08/2011 ዓ.ም |
| 9 | ነኢማ አወል | ሴ | | | |
| 10 | አህመድ መሃመድ | ወ | | | |
| 11 | አለም ደረጀ | ሴ | | | |
| 12 | ነሂማ ሀሰን | ሴ | | | |
| 13 | ሰሚራ ሽሪፍ | ሴ | | | |
| 14 | ፅዮን ደረጀ | ሴ | | | |
| 15 | ለሊሳ እምሩ | ወ | ቡድን-5 | 7 | 14/08/2011 ዓ.ም |
| 16 | ህይወት ትዕግስቱ | ሴ | | | |
| 17 | ነኢሙ ሱልጣን | ወ | | | |
| 18 | ነኢሙ ሻፊ | ወ | | | |
| 19 | አለማየሁ ድሪባ | ወ | | | |
| 20 | ቤተልሄም ታየ | ሴ | | | |
| 21 | ብርሃነመስቀል ዑልማ | ወ | | | |

# አባሪ 10

## በቡድን ተኮር ውይይት የተሳተፉ የእንግቢ ት/ቤት ተማሪዎች

| ተ/ቁ | ስም | ጾታ | መለያ | ብዛት | ውይይቱ የተካሄደበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሃዊ ቀነኒ | ሴ | ቡድን-6 | 7 | 15/08/2011 ዓ.ም |
| 2 | ድባባ ሀብታሙ | ሴ | | | |
| 3 | አዲሱ ለጋር | ወ | | | |
| 4 | ፋጡማ ተገኝ | ሴ | | | |
| 5 | ቢላል መሃመድ | ወ | | | |
| 6 | እንዳለ ያደታ | ወ | | | |
| 7 | አቤኔዘር አበበ | ወ | | | |
| 8 | ቸሩ አበበ | ወ | ቡድን 7 | 6 | 16/08/2011 ዓ.ም |
| 9 | ኦላንቱ አበራ | ሴ | | | |
| 10 | ረዲማ መሃመድ | ሴ | | | |
| 11 | ሬድዋን አህመድ | ወ | | | |
| 12 | ሀና ዋቅቶላ | ሴ | | | |
| 13 | ደራርቱ ተፈራ | ሴ | | | |
| 14 | ቦንቱ ከበደ | ሴ | ቡድን-8 | 6 | 17/08/2011 ዓ.ም |
| 15 | ከድር ታምሩ | ወ | | | |
| 16 | ንዋይ እዉነቱ | ወ | | | |
| 17 | ናዕፍ ዕዉነቱ | ወ | | | |
| 18 | ሀያት ዑመር | ሴ | | | |
| 19 | ኢያና አበበ | ወ | | | |

## አባሪ 11
## የቡድን ተኮር ዉይይት ተሳታፊዎች ልዩ ልዩ ፎቶ-ግራፎች

**ፎቶ-ግራፍ 1፡ ቡድን አንድ የቦረቻ ት/ቤት ተማሪዎች**



**ፎቶ-ግራፍ 2፡ ቡድን ሁለት የቦረቻ ት/ቤት ተማሪዎች**



ፎቶ-ግራፍ 3፡ ቡድን ሶስት የገቺ ት/ቤት ተማሪዎች



ፎቶ-ግራፍ 4፡ ቡድን አራት የገቺ ት/ቤት ተማሪዎች



ፎቶ-ግራፍ 5፡ ቡድን አምስት የገቺ ት/ቤት ተማሪዎች



ፎቶ-ግራፍ 6፡ ቡድን ስድስት የእንግቢ ት/ቤት ተማሪዎች



ፎቶ-ግራፍ 7፡ ቡድን ሰባት የእንግቢ ት/ቤት ተማሪዎች



ፎቶ-ግራፍ 8፡ ቡድን ስምንት የእንግቢ ት/ቤት ተማሪዎች

